# የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ

## ገንዘብ ሚኒስቴር (ገሚ)

2014-2018

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ

ገንዘብ ሚኒስቴር (ገሚ)

2014-2018

ይህ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ በመጀመሪያ በ2013 ዓ.ም. በዩኤን ዉመንና (UN Women) በኢትዮጵያ የገንዘብ ሚኒስቴር ትብብር ታተመ። በዚህ ህትመት የተገለጸው ሀሳብ የአጥኚው አመለካከት እንጂ የተቋማቱን አመለካከት የሚወክል አይደለም።

የዚህን ህትመት ይዘት ትክክለኛነት እውነተኛነት ብሎም ከተለያዩ ጽሁፎች የተወሰዱ ሀሳቦች በተገቢ ሁኔታ ምንጫቸውን ለመጥቀስ የተደረገውን ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኤን ዉማንና የኢትዮጵያ የገንዘብ ሚኒስቴር ስለህትመቱ ይዘት ትክክለኛነት ሀላፊነትን አይወስዱም። በተጨማሪም ቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የስትራቴጂውን ፍሬ ሀሳብ ወይም ይዘት በመጠቀም ብሎም ወደ ሌሎች ቋንቋዎች በመተርጎም ሂደት ላይ ምናልባት ሊፈጠር ስለሚችል ስህተት ሀላፊነት አይወስዱም።

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። በኢትዮጵያ የታተመ።

# የሚኒስትሯ መልእክት

ሰላም ጤና ይስጥልኝ፡-

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ከኢትዮጵያ መንግሥት ዋና የፖሊሲ ዓላማዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ከሌሎች ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር በመዋሃድ የፖሊሲ ውጤታማነትን የሚያጠናክርና ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ ልማት እንዲኖር የሚያደርግ ነው ። በማክሮ-ኢኮኖሚያዊ እና በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ የፋይናንስ ሥርዓት መኖር፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ሰፋ ያለ የፊስካል ፖሊሲን ፣ የውጭ ሀብት ማሰባሰብን ፣ የመንግሥት እና የግል አጋርነትን እንዲሁም የመንግሥት ፋይናንስ ማሻሻያዎችን የሚሸፍን ብሔራዊ ፖሊሲን ለማዘጋጀት ሃላፊነት እንዳለበት የፌደራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር በድርጅቱ ውስጥም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የማሳደግ እና ሴቶችን የማጎልበት ፍላጎት አለው።

የሴቶችን እውነተኛ አቅም አሟጦ ለመጠቀም እና በማክሮ-ኢኮኖሚያዊ እቅድ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማእከል አድርጎ ለማቀድ፣ ከብሔራዊው የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ጋር በጥሩ ሁኔታ የተጣጣመ የመካከለኛ ጊዜ ስትራቴጂ ፣ አገር በቀል የሆኑ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እና የሚኒስቴሩ የአምስት ዓመት ስትራቴጃዊ ዕቅድ አስፈላጊ ነበር። የገንዘብ ሚኒስቴር የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂን የማዘጋጀት ረጅምና ጠንከር ያለው ሂደት ፍሬ በማፍራቱ ደስተኛ ነኝ። ይህ ፋና ወጊ እና የተቀናጀ ስትራቴጂ፣ በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ፣ በፊስካል ፖሊሲ ዲዛይንና አተገባበር ፣ በመንግስትና በግል አጋርነት እና በኢኮኖሚ ትብብር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ መሰረት ይጥላል።

የኢትዮጵያ መንግስት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሰብአዊ መብት ፣ የዴሞክራሲ እና የፍትህ ጉዳይ እንጂ ለሴቶች የተሰጠ ስጦታ አለመሆኑን እውቅና መስጠቱ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት የተረጋገጠ ሀቅ ነው። በተጨማሪም፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ለሠራተኛ ገበያ ዕድገት ፣ ለማኅበራዊ ደህንነት ፣ ለሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ቅድመ ሁኔታ ነው።

መንግሥት ወደኋላ የሚጎትቱ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎችን እና አወቃቀሮችን በሚዋጋ የፖሊሲ አጀንዳ በመታገዝ፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማጎልበት ቁርጠኛ ነው። በተጨማሪም ፣ በሕብረተሰባችን ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማጎልበት፣ ለዚሁ ዓላማ በቂ የሆኑ ሀብቶችን መመደብ አለብን። እንደ መንግስት፣ እኛ አሁን ለውጦችን የማምጣት እና ልጃገረዶች እና ወንድ ልጆች ፣ ሴቶች እና ወንዶች በህብረተሰቡ ውስጥ የራሳቸውን ህይወት ለመቅረፅ ተመሳሳይ ስልጣን እና እድል የተሰጣቸው፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነበት ማህበረሰብ የመፍጠር ግባችንን ለማሳካት ያለንን ፍላጎት እያሳደግን ነው።

ስለሆነም የመንግስት ፋይናንስ እና የአመራሩ ለውጥ፣ መንግስት የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ ልማት አጀንዳን ተግባራዊ ለማድረግ ለሚያደርገው ጥረት ወሳኝ አካል ነው። ከዚህ አንፃር የመንግስት ፋይናንስ እና የበጀት ሂደት የመንግስትን ፖሊሲ እውን ለማድረግ ቁልፍ ፋይዳ ያላቸው ናቸው፤ ስለሆነም የፖሊሲ አቅጣጫን ወይም የሀብት ክፍፍልን በተመለከተ ውሳኔዎች ሲወሰዱ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ክፍሎች፣ ሁሉንም ሴቶችን የማጎልበት እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ጥረቶችን እንደ ዋና ሥራቸው በባለቤትነት በመውሰድ፣ የአስተባባሪነት ሚና ካለው የሴቶች ፣ ሕፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ጋር በቅርበት መሥራት አለባቸው ።

ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ የበጀት አሰራር ላይ ያለን አዲሱ ትኩረታችን ፣ ከብዙ በጥቂቱ፣ የተጠናከረ እና ሰፋ ያለ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ትንተና ማድረግን ፣ በጾታ የተለዩ ስታትስቲክሶችን የበለጠ ስልታዊ በሆነ መንገድ መጠቀምን እና ሴቶች እና ልጃ ገረዶች ፍትሃዊ የሀብት ተደራሽነት እንዲኖራቸው የተጠናከረ አፅንዖት ማድረግን የሚያስችሉ ውጤቶችን ያመጣል። የመንግስት ፋይናንስ እና አስተዳደሩ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ዓላማዎቻችን አስተዋፅዖ የሚያደርጉና፣ እድገት ፣ ዘላቂ ልማት እና ማህበራዊ ፍትህ እንዲፈጠር ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አልመናል።

ይህ ስትራቴጂ ሁሉም ተዋንያን የበለጠ የሥርዓተ-ፆታ ለውጥን ባገናዘበ መልኩ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እድል ይሰጣቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች፣ የአገሪቱ የወደፊት ኢንቬስትሜቶች ናቸው። የሀገሪቱ ግማሹ ሃይል እንዲያንሰራራ ዕድል ሊኖረው ይገባል።

በመጨረሻም በስትራቴጂው ዝግጅት ላይ የተሳተፉትን ሁሉ፣ በተለይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደቱን የመራውን የሥርዓተ-ፆታ ዳይሬክቶሬትን አመሰግናለሁ። እንዲሁም ዩኤን ዉመን (UN Women) አስፈላጊውን የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረጉ አድናቆቴን መግለፅ እፈልጋለሁ።

አመሰግናለሁ።

የተከበሩ ያስሚን ወሀብረቢ

የውጭ ኢኮኖሚ ትብብር ፣ ሚኒስትር ዴኤታ

የገንዘብ ሚኒስቴር (ገ/ሚ)

# Contents


1. መግቢያ 1
1.1 ታሪካዊ ዳራ 2
1.2 የስትራቴጂ ዕቅድ አላማ 4
1.3 የስትራቴጂ ዕቅድ ወሰን 4
1.4 የስትራቴጂክ ዕቅዱ ጠቀሜታ 5
2. የመስሪያ ቤቱ ታሪካዊ ዳራ 6
2.2 የመስሪያ ቤቱ ታሪካዊ ዳራ 7
2.1 የገንዘብ ሚኒስቴር (ተልእኮ፣ ራዕይ) 7
2.2 የገንዘብ ሚኒስቴር የሴቶች የህፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት 7
2.3 ያለፉት 5 አመታት አፈፃፀም 7
3. ቁርጠኝነት፣ ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ 9
3.1 ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ጋር በተያያዘ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች 10
3.2 ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎች እና ተያያዥ ሌሎች ሰነዶች 10
3.3 ሥርዓተ-ጾታን በሚመለከት የተገቡ ቃል ኪዳኖች እና በአፈፃፀማቸው መካከል የሚታይ ክፍተት 12
4. የነባራዊ ሁኔታ ትንተና 14
4.1 ሀገራዊ ሁኔታ እና ዋና ዋና ሂደቶች-በሀገራዊ ደረጃ 15
4.2 የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን በሚመለከት የገንዘብ ሚኒስቴር ያለበት ሁኔታ 17
5. ትንተና 19
5.1 ጥንካሬ፣ ድክመት፣መልካም አጋጣሚ፣ ስጋት እና የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ ትንተና 20
5.2 የባለድርሻ አካላት ትንተና 25
ምስል 1- የሥርዓተ-ጾታ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት-ተጽዕኖ ማትሪክስ 25
6. የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ- ዋና ምሰሶዎች፣ የሚጠበቁ ውጤቶች እና ቁልፍ ጣልቃ ገብነቶች/ አቅጣጫዎች/እርምጃዎች 29
6.1 እስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች 30
RESULT FRAMEWORK 36
ስትራቴጂክ ዓላማዎች፣ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና አመልካቾች
07. ክትትል እና ግምገማ 41
08. ግንኙነት 43
በስትራቴጂው የባለድርሻ አካላት ዝርዝር 45

# Contents

| | |
|---|---|
| AU | የአፍሪካ ህብረት |
| BPA | የቤጅግ የድርጊት መድረክ |
| CEDAW | በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ሁሉንም ዓይነት የመድል ዓይነቶች ለማስወገድ የሚያስችል ስምምነት |
| ECMP | የወጪ ቁጥጥር እና አያያዝ ፕሮግራም |
| GAD | የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዩች ዳሬክቶሬት |
| GDP | ጠቅላላ የሀ ገር ውስጥ ምርት |
| GES | የስረአተ-ፆታ እኩልነት እስትራቴጂ |
| GEWE | የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና ሴቶች ማብቃት |
| GRB | የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት |
| GTP | የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ |
| IFMIS | የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር እና የመረጃ ስርዓት |
| IMF | ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት |
| M&E | ክትትል እና ግምገማ |
| MDG | የሚሊኒየም ልማት ግብ |
| MoF | የገንዘብ ሚኒስቴር |
| MoWCY | የሴቶች ልጆችና ወጣቶች ሚኒስቴር |
| NAP-GE | በፆታ እኩልነት ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር |
| ODA | ኦፊሴላዊ የልማት ረዳት |
| OECD-DAC | ለኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት-ልማት እርዳታ ኮሚቴ |
| PB | የፕሮግራም በጀት |
| PBS | የመሠረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት |
| PESTEL | ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ቴክኖሎጂ ፣ አካባቢያዊ እና የህግ ትንተና |
| PFM | የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር |
| PPP | የመንግስት የግል አጋርነት |
| SWOT | የጥንካሬ ፣ድክመቶች፣ ዕድሎች እና ስጋቶች |
| SDGs | ዘላቂ የልማት ግቦች |

# 01.

# መግቢያ

## 1.1 ታሪካዊ ዳራ

በኢትዮጵያ ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ምላሽ ሰጪ የሆነ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መኖር ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነትና ኢኮኖሚያዊ ሽግግር ለማምጣት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ምክንያቱም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማረጋገጥ በራሱ ዋና እና ቁልፉ የፖሊሲ ግብ ሲሆን ከሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር በመሆን በሚፈጥረው ተጨማሪ ጉልበት ማህበራዊ ለውጥን ለማምጣት ይረዳል። በመሆኑም የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ዋናው ዓላማ የመንግስት ሀብት አጠቃቀምን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የመንግስት ፖሊሲ ማስፀፈሚያ ቀጣይነት እና ግልፅነት ባለው መልኩ እንዲሆን ይረዳል። ከማክሮ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ውስጥ አንዱ የፊስካል ፖሊሲ የመንግስት ወጪን እና ገቢን ተጠቅሞ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ለመፍጠር እና ለመቆጣጠር የሚጠቀምበት ነው። መንግስት ወጪን እና ገቢን የመቆጣጠር ስልጣኑን ተጠቅሞ እንደሚተገብረው እንደ ፖሊሲው አይነት ይለያያል ብዙዎቹ መንግስታት ቀጣይነት ያለው እድገት እና የተረጋጋ ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍል በማምጣት ድህነትን ለመቀነስ ይጠቀሙበታል (MoF, 2018)።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ የፊስካል ፖሊሲ ዋና አላማ ቀጣይነት ያለው ፈጣን እና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እና በተጨማሪነት የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ መሳሪያ ነው። ሆኖም ግን ከላይ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የፊስካል ፖሊሲ መገለጫ እና ትንተናዎቹ ያለውን የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ከድህነት አዙሪት ውስጥ ማውጣት አለመቻሉ ነው። የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት በሁለቱም በኩል ማለትም በራሱ የልማት ግብ እና ለልማት ግብ ስኬት እንደ ቅድመ ሁኔታ ይታያል።

በመሆኑም የፊስካል ፖሊሲ እንደ ሌሎች የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ስማርት ኢኮኖሚክስ እና የሰብአዊ መብትን ያካትታል፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማምጣት የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በመጨመር ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማምጣት የተሻሻለ የሴቶች እና የህፃናት ጤና የግብ ስኬትን ያመጣል (Kolovich, 2018) ። ላለፉት አስርተ አመታት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት ተግባር መሻሻሎችን እያሳየ ነው። የ1995 የቤጂንግ የድርጊት መድረክ የመንግስትን በጀት ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ እንዲሆን የሚወሰዱ እርምጃዎችን ቅንጅታዊ ውሳኔዎች በበጀት፣ በፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ላይ አስፈላጊውን ፋይናንስ በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ መመደብ በሴቶች እና ወንዶች መካከል እኩልነትን ለማምጣት ያስችላል።

በመሆኑም ዋናው ጉዳይ የመንግስት በጀት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማምጣት እየተተገበረ ባለመሆኑ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባር ላይ እንዲውል ለማገዝ ነው። ተጨባጭ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማበረታታት በራሱ ስማርት የኢኮኖሚክስ እሳቤ ቢሆንም የመንግስት ወጪ በስልታዊ መንገድ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማረጋገጥ ሳይችል ቀርቶ፣ ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እይታ ውጪ ሆኗል። እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ያሉ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት መንግስት ዋነኛ የልማት የፋይናንስ ምንጭ ነው። ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ምላሽ የማይሰጥ በጀት የመንግስት ወጪን ተጠቅሞ በህብረተሰቡ ውስጥ የሴቶችን ተጠቃሚነት የማሻሻል እድልን እንዳለመጠቀም ይቆጠራል። መንግስት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ፖሊሲውን ለመተግበር ወደ ኋላ እንደማይል ቢያሳይም እንደ የወጪ ቅነሳ ያሉ እርምጃዎች ላይ ቅነሳው ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ሊነካ ይችላል (Birchall and Fontana, 2015)፤ በተመሳሳይ እንደ ሽያጭ ታክስ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ያሉት ማሻሻያዎች ጫናው ሴቶች ላይ ያመዝናል።

በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች የታክስ አወቃቀር ለሴቶች ገለልተኛ ያለመሆን እና ፍላጎታቸውን ያላማከለ መሆን (Joshi, 2016)፤ መድሎ የሚመነጨው ከራሱ ከታክስ አወቃቀሩ በግልጽ ወይም ግልጽ ባልሆነ፣ በሚያስገቡት ገቢ፣ በገቢ ሰብሳቢ ሴቶች ወይም የገቢ ስብሳቢ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለምሳሌ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጫና ሴቶች ላይ የበረታ ይሆናል። እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ሴቶች የቤት ውስጥ መገልገያ ዋነኛ ገዢዎች ቢሆኑም፣ በመንግስትም ሆነ በትምህርት ባለሙያዎች ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ የሚፈጥረው ጫና አልታየም:: የመንግስት ፋይናንስ፣ የመንግስት ወጪ አስተዳደርን እና ሀብት አጠቃቀም ስልታዊ በሆነ መንገድ ተጠቅሞ የሥርዓተ-ጾታ አለመመጣጠንን መቀነስ ያስችላል።

ሥርዓተ-ጾታን ማእከል ያደረገ የፊስካል ፖሊሲ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ሊፈቱ የሚችሉ ሰፊ መሰረት ያላቸው እና የታለመ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ችግር ሊፈታ በሚችል መልኩ ሊቀረፅ ይችላል፡፡ በቀጥታ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን የሚረዱ ፕሮግራሞችን በእውቀት እና ቁሰቁስ አቅርቦት በመደገፍ በኢኮኖሚ የተጎዱትን ሴቶች ከኢኮኖሚ እና ከስራ አጥነት ችግሮች እንዲላቀቁ እና ተመሳሳይ ስር የሰደዱ እና ታሪካዊ የሆኑ የሴቶች ጭቆና እና ጥቃት ላይ የሚሰሩ ስራዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Kaufman, et al, 2019)። በተጨማሪም መንግስት ከፍተኛ ወጪ በሚመድብባቸው ዘርፎች ለሴቶች የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ እንደ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ ጤና ተቋማት መሰረተ ልማት አቅርቦት መንገድ እና ሌሎች አቅርቦቶች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን እና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና ያመጣል።

ሥርዓተ-ጾታን ያማከለ የመንግስት ወጪ ትግበራ ሴቶች ያለክፍያ የሚሰሯቸው እንደ ማገዶ ለቀማ እና ውሀ መቅዳት፣ የቤት ውስጥ ስራ እንደ ምግብ ማብሰል፣ ልጆች መንከባከብ፣ እድሜያቸው የገፋ ጡረተኞችን እና የታመሙትን መንከባከብ በመሳሰሉት ተግባራት ጫና እንዳለባቸው ከግንዛቤ ያስገባል (IMF, 2018)። ስለሆነም የመንግስት ወጪ/ፋይናንስ አስተዳደር ፖሊሲ እነዚህን እውነታዎች ማዕከል አድርጎ ልዩነቱን ለማስተካከል መዘጋጀት አለበት።

ኢትዮጵያ ለሴቶች እድገት ያላትን ቁርጠኝነት በ1993 ሀገራዊ የሴቶች ፖሊሲን በማዘጋጀት እና በ1995 በህገ መንግስቱ ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው የሴቶችን ችግር መፍታት እና እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው ያላትን ቁርጠኝነት አሳይታለች። በተጨማሪም ኢትዮጵያ የተለያዩ አለም አቀፋዊ እና ቀጠናዊ ስምምነቶችን በመፈረም ተሳታፊ የነበረች ሲሆን እነሱም የቤጂንግ የድርጊት መድረክ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ሁሉንም ዓይነት የመድል ዓይነቶች ለማስወገድ የሚያስችል ስምምነት (CEDAW)፣ ዘላቂ የልማት ግቦች (SDGs)። በተጨማሪ የአፍሪካ ህብረት ስትራቴጂ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ሴቶችን ማብቃት የሎሜ ስምምነት የሥርዓተ-ጾታእኩልነት በአፍሪካ እና ዳካር ፕላትፎርም ኦፍ አክሽን 1999 የተወሰኑት ኢትዮጵያ የተካፈለችባቸው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት መድረኮች ናቸው። ሴቶችን ማብቃትና ለዚሁ ስራ የሚውሉ ወጪዎችን ፋይናንስ ማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ሃላፊነት ነው፤ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሄንን ሃላፊነት ለመወጣት የፊስካል ፖሊሲ፣ የኢኮኖሚ ትብብር እና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን እንደ ዋነኛ መሳሪያ ይጠቀማል።

የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን በጀት ማዘጋጀት የውጪ ኢኮኖሚ ትብብር፣ የውጪ ሀብትን ማፈላለግ የፊስካል እና ሌሎች ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር ናቸው። በተመሳሳይ ሥርዓተ-ጾታን ማዕከል ያደረገ የፊስካል ፖሊሲ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ሊፈቱ የሚችሉ የተለያዩ ስትራቴጂካዊ ክፍተቶችን እና ስትራቴጂዎችን መንደፍ ዋናውን የእኩልነት ችግር ሊፈታ የሚችል የመንግስት ፋይናንስን ያማከለ እና ጠቋሚ የሥርዓተ-ጾታ ስትራቴጂን መተግበር ነው። በመሆኑም መሪ ተቋም እንደመሆኑ ካለበት ኃላፊነት አንፃር ፊስካል ፖሊሲ የውጪ ኢኮኖሚ ትብብር እና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር በአግባቡ የተጠናከረ SMART (የተወሰነ፣ ሊለካ የሚችል፣ የሚደረስበት፣ አስተማማኝ እና በጊዜ የተወሰነ) ጠቋሚ የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መንደፍ ችግሩን ለመፍታት ይረዳል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ መሰረት ስለሚያደርግ የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ማዕከል ሳያደርግ ይዘጋጃል ስለዚህ እነዚህ ፖሊሲዎች ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ቦታ የማይሰጡ ይሆናሉ። ነገር ግን ሰፋፊ የመንግስት ፖሊሲዎች ማለትም የፊስካል፣ የገንዘብ እና የንግድ ፖሊሲዎች በሴቶች እና በወንዶች ላይ የተለያየ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። የገንዘብ ሚኒስቴር መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች ስር ለሚቀረፁ ፕሮጀክቶች በጀት ይመድባል እና አስገዳጅ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማውጣት የታሰበው እንዲሳካ ያደርጋል። በአግባቡ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መኖር የፋይናንስ ባለስልጣንን የግብር እና የወጪ ፖሊሲውን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን እንደ መሳሪያ ተጠቅሞ ያለውን የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ችግር መፍታት እና በሴቶች ላይ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት ያስችለዋል።

## 1.2 የስትራቴጂ ዕቅድ አላማ

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂው ዋና አላማ መሰረት ያደረገው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን የሚያረጋግጥ የማእቀፍ ለውጥ በማምጣት ማለትም በመንግስት ፋይናንስና አስተዳደር፣ በፊስካል ፖሊሲና ትግበራ፣ በመንግስት እና በግል አጋርነት፣ በውጪ ሀብት ማፈላለግ፣ በኢኮኖሚያዊ ትብብር እና ጠንካራ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ናቸው፡ ፡ በአጠቃላይ ስትራቴጂውን ለማረጋገጥ የተፈለገው ሴቶች እና ወንዶችን በእኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ፊስካል ፖሊሲ ትግበራ፣ ማሻሻያ እና የመንግስት ወጪ መኖሩን ነው፡፡ ስትራቴጂው የሚመራው የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ በፖሊሲው ውስጥ ማሳለጥ እና በመ/ቤቱ የቀን ተቀን ትግበራ ውስጥ በማካተት

ነው፡፡

በመሆኑም ስትራቴጂው በዋናነት፡-

- ሴቶችን እንዴት በስልታዊ መንገድ የመንግስት ወጪን ተጠቅሞ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል፣
- በጀት አመዳደብን ተጠቅሞ የመንግስት ወጪን በሁሉም መ/ቤቶች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ለማሳካት ማዋል፣
- በኢትዮጵያ ሴቶች ከኢኮኖሚያዊ ትብብሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማመቻቸት፣
- የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን ከውጪ ሀብት ማፈላለግ ጋር በማሳለጥ የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነት እና ማስፈፀሚያ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- የፊስካል ፖሊሲ እድገት ጥናት እና ማስፈፀሚያ ሂደቶቹ ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ምላሽ ሰጪ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የፋይናንስ ዘርፍ ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ምላሽ ሰጪ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ስማርት ኢኮኖሚክስ እሳቤን ማረጋገጥ፣

## 1.3 የስትራቴጂ ዕቅድ ወሰን

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ዕቅድ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በሌሎች ተቋማት የሚወጡ ፖሊሲዎች የሴቶችን እኩል ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ስፋት በገንዘብ ሚኒስቴር ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት እና ዘርፉ ያለው ተደራሽነት መሰረት ያደርጋል:: በመሆኑም በፌደራል ደረጃ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት እና ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህገ መንግስት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተሰጠው ሃላፊነት በማእከላዊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ከተሰጡት ሃላፊነቶች ውስጥ ፋይናንስ ነክ ጉዳዮችን ማስተዳደር እና መቆጣጠር በጀትን ማዘጋጀትና ማስተዳደር ሀብትን ማስተዳደር፣ ፊስካል ፖሊሲ ማውጣት ናቸው፡፡ የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ለመንደፍ የባለ ድርሻ አካላትን ለመለየት ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች የበጀት ድርሻ ከኢኮኖሚ እድገት ቀጥተኛ ተጠቃሚነት አገራዊ እቅድ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ክልሎች የስራ ክፍሎች ያላቸው ትስስር፤ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊነቶች እና ለወደፊት የሚኖራቸው ተሳትፎ ወዘተ፡፡ በተመሳሳይ ስትራቴጂ ፕላኑ አገራዊ የልማት ራእይ፣ የ10 አመት መሪ እቅዱን፣ የመስሪያ ቤቱን የ5 አመት ስትራቴጂ እቅድ መሰረት በማድረግ በ5 (አምስት) አመት ውስጥ የሚተገበር ይሆናል፡፡

## 1.4 የስትራቴጂክ ዕቅዱ ጠቀሜታ

የማክሮ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ማእከል ሳያደርግ ይዘጋጃል በብዛት እነዚህ ፖሊሲዎች የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን ከግምት ያስገቡ አይደሉም፡፡ ነገር ግን ሰፋፊ የመንግስት ፖሊሲዎች ማለትም የፊስካል የገንዘብ እና የንግድ ፖሊሲዎች በሴቶች እና በወንዶች ላይ የተለያየ ተፅእኖ ያሳድራሉ፡፡ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ላይ ትኩረት ማድረጉ ምክንያቱም በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ውስጥ የሴቶች መብት ለማረጋገጥ ገቢ ያላቸው ሴቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የሚወጡ ፖሊሲዎች የሥርዓተ-ጾታ

አለመመጣጠንን እንዲቀንሱ እና ያለ ክፍያ የሚሰሩ ሴቶችን ፍላጎት ያካትታል። የማክሮ ኢኮኖሚ ውሳኔዎች በወንድ እና በሴት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደር የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያስከትሉ ይችላሉ (UNWOMEN, 2016)::

ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት የፋይናንስ ባለስልጣንን የግብር እና የወጪ ፖሊሲውን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን እንደ መሳሪያ ተጠቅሞ ያለውን የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ችግር መፍታት እና በሴቶች ላይ የማህበራዊ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት ያስችለዋል (Budlender and Hewitt 2003; Budlender and Sharp 1998; Elson 2003; Kolovich, 2018, Stotsky 2006, 2016; IMF, 2017, 2018)። በመሆኑም ሥርዓተ-ጾታን በፊስካል ፖሊሲ እና በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የሃብት ማሰባሰብን ጨምሮ (የውጭ እና የአገር ውስጥ) ማሳለጥ ጠንቃቃ የማክሮ ኢኮኖሚ በመፍጠር የሴቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ያሻሽላል።

በማዕከላዊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ከተሰጡት ኃላፊነቶች ውስጥ በጀትን ማዘጋጀትና ማስተዳደር፣ሀብትን ማስተዳደር፣ ፖሊሲ ማውጣት፣ የመንግስት ፋይናንስ ማስተዳደር፣ የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መንደፍና ንቁ ህብረተሰብ መፍጠር ይገኙበታል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ሪፎርም እያቀደችና እየተገበረች ትገኛለች አዲሱን ምዕራፍ የ10 (አስር) አመት ጠቋሚ የእድገት እቅድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመሪነት እና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ የነቃ ተሳትፎ ያደርጋል።

በተጨማሪም ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ በመንግስት እና በግል አጋርነት በትብብር እየሰራች ወደፊት የግሉ ዘርፍ የመሪነት ሚና የሚጫወትበት እና የእድገት ምንጭ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል። ነገር ግን የመንግስት እና የግል አጋርነት ፖሊሲዎች እና ማስፈፀሚያዎቹ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው እንደ ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚክ ማሻሻያዎች ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ምላሽ የሌለው ሆኗል። በመሆኑም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስፈለገበት ምክንያት ክፍተቶችን በመለየት ጠቃሚ የሆኑ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በሴቶች እና ወንዶች ተግባራዊ ተሳትፎ በማክሮ ደረጃ ያለውን ክፍተት ለመቀነስ ነው።

በተጨማሪም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ መኖሩ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ፊስካል ፖሊሲ መሳለጡ እና አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ጋር መቀናጀቱ ለሚቀጥለው ስትራቴጂ ለ 10 (አስር) አመት ለሚዘጋጀው መሪ እቅድ ሥርዓተ-ጾታ ራሱን ችሎ ከሌሎች ጋር በማሳለጥ እንደ አንድ ምሰሶ ሆኖ ይካተታል።

# 02.

## የመስሪያ ቤቱ ታሪካዊ ዳራ

## 2. የመስሪያ ቤቱ ታሪካዊ ዳራ

### 2.1 የገንዘብ ሚኒስቴር (ተልእኮ፣ ራዕይ)

ኢትዮጵያ ድህነት ተኮር ፖሊሲ የልማት እቅድ እና ፕሮግራሞች ከድህነት ለመውጣት እና ዘላቂ ልማት ለማስመዝገብ ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች እየተገበረች ትገኛለች፤ ነገር ግን አለም በፍጥነት እየተቀያየረ ባለበት ወቅት እነዚህን አጋጣሚዎች መጠቀም ያስፈልጋል። ለዚህም እንደ ሀገር ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣ለዚህም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገራዊ የልማት እቅድ እና ፋይናንስ ላይ ካለበት ሃላፊነት አንፃር ለውጥ ማምጣት እንደሚችል ይታመንበታል፡፡

በዚህ እሳቤ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተልእኮ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች በማስተካከል በፌደራል ደረጃ በሚሰጠው አገልግሎት ቀዳሚ የልህቀት ማዕከል በመሆን ዋና ዋና ግቦች፡-

- ተቋማዊ ግንባታ፣
- የፊስካል ፖሊሲ፣
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን እና
- ሀብት ማፈላለግ እና የኢኮኖሚ ትብብር የተሰጠውን ሃላፊነት ከግብ ለማድረስ እንደ ዋነኛ መሳሪያ ይገለገልበታል።

በተመሳሰይ የገንዘብ ሚኒስቴር ኃላፊነት ከክልሎች ጋር በመሆን የኢኮኖሚ ትብብር ፖሊሲዎች ማውጣት በዋናነት ለታክስ እና ቀረጥ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ፤ የበጀት፣ ሂሳብ፣ የክፍያ፣ የውስጥ ኦዲት፣ የግዢ እና ንብረት አስተዳደር በፌደራል መንግስት ደረጃ እና በክልሎች የተጣጣመ ስርዓት መዘርጋት እና አፈፃፀማቸውን ክትትል ማድረግ። በተጨማሪም የፌደራል መንግስት በጀት ማዘጋጀት በፀደቀው በጀት መሰረት ክፍያ መፈፀምና አፈፃፀሙን መከታተልና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የሁለትዮሽ የእርዳታ እና ብድር የትብብር ስምምነቶችን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሊጠቅም በሚችል መልኩ መዋዋል እና አፈፃፀማቸውን መከታተል ነው።

### 2.2 የገንዘብ ሚኒስቴር የሴቶች የህፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

የዳይሬክቶሬቱ ተግባር እና ኃላፊነት ለመስሪያ ቤቱ ከተሰጡት የሚመነጭ ይሆናል፤ ከአገራዊ የፋይናንስ ስርዓት አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሴቶች ተጠቃሚነት ከማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትግበራ ማረጋገጥ ይሰራል፡፡ በመሆኑም ዋናው የዳይሬክቶሬቱ ሃላፊነት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት ጋር በሚገባ ተጣጥሞ ሁሉም ፖሊሲዎችና እርምጃዎች የሴቶችን ትክክለኛ ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጡ ማስቻል ነው።። ዋነኛው የዳይሬክቶሬቱ ኃላፊነት በሴክተሩ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ የእድገት ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ እንዲሁም የሌላ ዘርፍ ፖሊሲዎችን በመፈተሽ በመገምገም ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

በተመሳሰይ ዳይሬክቶሬቱ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት አሰራር ያመጣውን ውጤት እና ለውጥ የመገምገም፣ እና ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት አሰራርን ለማሳለጥ የአቅም ግንባታ ስራዎችን፣ መመሪዎችን እና ስልጠና ለባለ ድርሻ አካላት ማለትም ለባለ በጀት መስሪያ ቤቶች፣ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እና ለክልል ቢሮዎች ወዘተ እና ሌላኛው የዳይሬክቶሬቱ ሃላፊነት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በዘርፉ እና በመስሪያ ቤት ደረጃ ማረጋገጥ ነው።

በጀት በዋናነት የመንግስት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ በመሆኑ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የምንጠቀምት መሳሪያ ነው። ዳይሬክቶሬቱ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመሆን የበጀት ጥያቄ መገምገም፣ በጀት ስሚ ወቅት መሳተፍ ጥያቄ ማንሳት እና ከመስሪያ ቤት ፕሮግራም ክትትልና ቅንጅት ማድረግ እና ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ላይ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራት እና የስራ ግንኙነት በመፍጠር ከኢኮኖሚ ዘርፍ የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የተቋሙ ሴት ሠራተኞች ባላቸው አቅም መጠቀም እንዲችሉ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመተባበር የትምህርት እና የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣ በጾታ የተከፋፈለ የሠራተኞች መረጃ በማሰባሰብ ሴቶች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ያሉበትን ደረጃ ጥናት ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 2.3 ያለፉት 5 አመታት አፈፃፀም

ኢትዮጵያ ባለፉት አስርተ አመታት አመርቂ የሚባል እድገት አስመዝግባለች የገንዘብ ሚኒስቴር ለዚህ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ባለፉት አምስት አመታት የገንዘብ ሚኒስቴር ሀገሪቱ ላስመዘገበችው ተከታታይነት ያለው ማህበራዊ እና ኢኪኖሚያዊ እድገት መሳካት አስተዋጽኦ አለው፣ በተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት ሀገራዊ የልማት እቅድ ስኬት ለማሳካት የሚያስችል የመንግስት ገቢ በአማካኝ 19.3 በመቶ እድገት ባለፉት 5 አመታት አስመዝግቧል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ገቢ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ባለፈው 5 እና 10 አመታት በተከታታይ የተመዘገበው የገቢ እድገት የዚህ ውጤት ነው። ነገር ግን የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት እድገት ያለው ምጣኔ ለረጅም ጊዜ ከ12 በመቶ ከፍ ማለት ሳይችል ባለፉት 5 አመታት ቅናሽ አሳይቷል። ይህ ዝቅተኛ ቁጥር ከሰሃራ በታች ከሚገኙ ሀገራት አማካኝ ያነሰ ሲሆን የአለም ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው 15 በመቶ ነው። የፌደራል መንግስት ወጪ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማት ፕሮግራሞች እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ፣ ግብርና እና መንገድ በአማካኝ የ22 በመቶ እድገት ጭማሪ አሳይቷል።

የገንዘብ ሚኒስቴር ሁሉንም መደበኛ ወጪዎች በሀገር ውስጥ ገቢ የሚሸፈን ሲሆን፣ አብዛኛውን የካፒታል ወጪ በውስጥ ገቢ ለመሸፈን ይሰራል። የወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ሪፎርም ፕሮግራም በበጀት ዝግጅትና አስተዳደር፣ ክፍያ፣ ሂሳብ የውስጥ እና የውጪ ኦዲት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ስርዓት መደገፍ /በፌደራል ደረጃ/፡፡ በተጨማሪም መንግስት በሚያወጣው አቅጣጫ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር የእዳ ጫናን ለማቃለል ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ ይሰራል እነዚህም ለጊዜው የንግድ እዳዎችን ክፍያ ማቋረጥ፣ ከአበዳሪዎች ጋር የእፎይታ ጊዜ ለማራዘም መደራደር (ለምሳሌ ከቻይና መንግስት)።

የገንዘብ ሚኒስቴር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ይተገብራል፤ ለስራ እድል ፈጠራ ከግብርና ማምረቻ /Manifacturing/ ዘርፍ ጋር የተያያዘ እና የኤክስፖርት ገቢዎች የገቢ ንግድ ወጪን እንዲሸፍን የልማት ፕሮጀክቶችን ከውስጥ አቅም በተጨማሪ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ፣ ከሀገራት እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች በብድር፣ እርዳታ (የገንዘብ ቴክኒካል)፣ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ድጋፍ ያደርጋሉ። ከመንግስት እና የግል አጋርነት ጋር ተያይዞ ያለው አቅም ለመጠቀም ያሉት ክፍተቶች በመለየት ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስልጠና እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ይሰራል።

በመንግስት መስሪያ ቤቶች የህፃናት ማቆያዎችን ለመገንባት በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የህፃናት ማቆያ ግንባታው ተጠናቋል። ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከመጣ ልዑክ ጋር በሥርዓተ-ጾታ እና የማክሮ ኢኮኖሚ ላይ የልምድ ልውውጥ የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፣ ልዑኩም የአቅም ግንባታ ስራውን በስልጠና እና ሞዴል ልምምዶችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ከሌላ መስሪያ ቤቱ ለተውጣጡ ሰራተኞች ተሰጥቷል። ሁለት ሞዴል ተቋማትን ማለትም (ግብርና ሚኒስቴር እና የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ) በመውሰድ የሥርዓተ-ጾታ በጀቲንግ ክትትል የበጀት ልምምድ ተደርጓል። ወጣቶች እና ሴቶችን ለማብቃት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለ 119 ሴት እና 11 ወንድ ሰራተኞች ተካፍለዋል እርስ በርሳቸው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ተደርጎል።

ሴቶችን ማብቃት እና እኩልነት በመንግስት ፋይናንስ ዙሪያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ4 አመት ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት የሚከተሉትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የእድገት አጀንዳዎች አካቷል፡-

- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ውስጥ በጾታ የተከፋፈለ የፋይናንስ መረጃ ተጠቅሞ እኩል ተጠቃሚነት ማረጋገጥ
- በፕሮግራም በጀት ውስጥ ሥርዓተ-ጾታን ለማካተት ጥሩ ተሞክሮ አለ
- የተቀመጠውን ግብ የሚለካ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት
- የበጀት የወጪ እና ሌሎች ዋና ዋና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ በተለያየ መልኩ ማዳረስ
- የመሰረተ ልማት አውታሮች (ትምህርት፣ ጤና፣ ኤሌክትሪሲቲ እና ውሃ) የልማት ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው ባለፉት 5 አመታት ተተግብረዋል
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂ ግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ውጤት ተኮር ተደራሽነትና፣ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ

# 03.

# ቁርጠኝነት፣ ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ

## 3.1 ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ጋር በተያያዘ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሥርዓተ-ጾታ እና ሴቶችን የማብቃትጉዳይበመንግስታትደረጃትኩረትማግኘት የጀመረው እ.ኤ.አ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። የሪዮ ዲጄኔሪዮ የአካባቢ እና የልማት ዲክላሬሽን መርህ ቁጥር 20 ቀጣይነት ያለው ልማትን ለማስመዝገብ የሴቶችን ሚና በጉልህ አሳይቷል። በተጨማሪም በ1995 የወጣው The Beijing Declaration and Platform for Action መንግስታት የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን በፖሊሲዎቻቸው እና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ እንዲሁም ለሴቶች የተለየ ጥቅም የሚሰጡ ፕሮግራሞች ላይ ሀብት እንዲመድቡ ጥሪ አድርጓል። በሴቶች ላይ የሚፈፀምን ማንኛውም ዓይነት መድሎ ለማጥፋት የተደረገው ዓለም አቀፍ ስምምነት በብዙ ሀገሮች የተፈረመ እና እ.ኤ.አ በ1981 ወደ ተግባር የገባ ሲሆን ስምምነቱ የሥርዓተ-ጾታ አለመመጣጠን በሴቶች ላይ ከሚደርስ መድሎ የሚመነጭ ሲሆን መንግስታት ችግሩን ለመቅረፍ በተግባር መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡ ሌላኛው ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን እ.ኤ.አ የ1993ቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የማስቆም ስምምነት ሲሆን ይህ ስምምነት በሴቶች ላይ ለሚደርስ ጥቃት ትኩረት የሰጠ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግ ነው። በተመሳሳይ የካይሮ የስነህዝብ እና ልማት ዲክላሬሽን የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ማብቃት ድህነትን ከማጥፋት፣ የህዝብ ቁጥር ዕድገትን ከመቆጣጠር እና የልማትን ቀጣይነት (Sustainable Developmnt) ከማረጋገጥ አንፃር ያለው ሚና ዕውቅና የተሰጠበት ሌላኛው መድረክ ነው። የሚሊኒየም የልማት ግቦች የሥርዓተ-ጾታ አለመመጣጠን ዕውቅና የሰጠ እና እንዴት መለወጥ እንደሚቻል አቅጣጫ ያስቀመጠ ሌላው ዓለም አቀፍ ውል ነው። ስለሆነም የሚሊኒየሙ የልማት ግብ ከዚህ ቀደም የነበሩ ሰነዶችን በማካተት ታርጌቶችን በዕቅድ መልክ ያስቀመጠ ሰነድ ነው። በአሁኑ ሰዓት ዘላቂ የልማት ግቦቹ ሴቶች የማብቃትን ጉዳይ እንደ አንድ አጀንዳ ሲያስቀምጥ ማንንም ወደ ኋላ አለመጣል በሚለው መርህ ውስጥ በማካተት የሥርዓተ-ጾታ ዕኩልነት በዘላቂ የልማት ግቦች 2030 ውስጥ እንደ አንድ ግብ የተካተተ ሲሆን በአምስተኛው ግብ ማለትም በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚፈጸመውን መድሎ ማስቆም በሚለው ግብ ስር ተካቷል። በቀጠና ደረጃም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም መድሎ ለማስቆም የሚረዱ የተለያዩ ውሳኔዎች፣ ፕሮቶኮሎች፣ ቃልኪዳኖች እና የድርጊት መርሀ ግብሮች ተቀርፀው በትግበራ ላይ እንዳሉ ይታወቃል። ከነዚህም መካከል ሴቶች በሁሉም መስክ የሚኖራቸውን ምርጫ የሚመለከተው የማፑቶው ፕሮቶኮል ይጠቀሳል፡፡ ይህ ፕሮቶኮል በአፍሪካ የሴቶች እና በአጠቃላይ ሰብዓዊ መብትን ለማስጠበቅ ዋነኛው የህግ ሰነድ ነው። የአፍሪካ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት መሃላ (The Solemn Declaration on Gender Equality in Africa) በአፍሪካ ህብረት ጉባኤ እ.ኤ.አ በ2004 ዓ.ም. ተቀባይነትን ያገኘ ሲሆን ዲክላሬሽኑ አባል ሀገራት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ እና በዓለም አቀፍ፣ ቀጠናዊ እና በሀገር ደረጃ ሌሎች የተለያዩ ፕሮቶኮሎችን ለመፈረም ያላሰለሰ ጥረት ማድረግን ያካትታል።

ከማፑቶ ፕሮቶኮል እና የአፍሪካ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት መሃላ በተጨማሪ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ በአህጉር ደረጃ የተለያዩ ቃል ኪዳኖች ተገብተዋል። ከነዚህም መካከል እ.ኤ.አ በ1994 የተፈረመው የዳካር ፕላትፎርም ፎር አክሽን፣ እ.ኤ.አ በ1999 የተፈረመው እና የዳካሩን እና የቤጂንጉን ስምምነቶች ትግበራ በማቀላጠፍ የሴቶችን ህይወት መለወጥ ዓላማ ያደረገው ስምምነት፣ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም. የተፈረመው እና የአፍሪካ የሰብዓዊ እና የሰዎች መብቶች እንዲሁም በሴቶች መብቶች ላይ ትኩረት ያደረገው ቻርተር፣ እና እ.ኤ.አ በ2004 የተፈረመው በሴቶች ላይ ትኩረቱን ያደረገው ሰባተኛው የአፍሪካ ቀጠናዊ ኮንፈረንስ ዋነኞቹ ናቸው። ኢትዮጵያም የማፑቶን ፕሮቶኮል ጨምሮ በእነዚህ ዓለም አቀፍ እና ቀጠናዊ ስምነቶች ላይ ተሳታፊ እና ፈራሚ ነች።

## 3.2 ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎች እና ተያያዥ ሌሎች ሰነዶች

የኢትዮጵያ መንግስት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን እና ሴቶችን ማብቃት ላይ የሚተገበሩ ተግባራትን ለማቀላጠፍ የሚረዱ የተለያዩ ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ ቁርጠኝነቱን አሳይቷል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ዓለም አቀፍ እና ቀጠናዊ የሥርዓተ-ጾታ ስምምነቶችን ከመፈረም በተጨማሪ በሀገር ደረጃ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች እና የድርጊት መርሃ ግብሮች ተቀርፀው በትግበራ ላይ እንደሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ተገምግመዋል።

**የ1993ቱ ብሔራዊ የሴቶች ተጠቃሚነት ፖሊሲ:** በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ብሔራዊ የሴቶች ፖሊሲ የተቀረፀው እ.ኤ.አ በ1993 ሲሆን ዓላማውም በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መስክ የሴቶችን ጥቅም እና ተሳትፎ ለማረጋገጥ ነው። በተጨማሪም ፖሊሲው በሀገሪቱ በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች

ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በቅንጅት እኩል ተሳትፎ እንዲያደርግ ያለው ፍላጎት የተረጋገጠበት ነው፡፡

**የ1995ቱ የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት:** የ1995ቱ ህገ መንግስት መጽደቅ በሀገሪቱ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንፃር ትልቅ ክስተት ነው፡፡ የዚህ ህገመንግስት አንቀፅ 25 ሁሉም ሰብዓዊ ፍጡራን በህግ ፊት ካለምንም መድልዎ እኩል እንደሆኑ እና የህግ ከለላ እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይህ ሀገ-መንግስት ሴቶች ንብረት ማፍራት፣ የስራ ዕድል እና የወሊድ ፍቃድን ጨምሮ ከወንዶች እኩል መብት እንዳላቸው አስቀምጧል፡፡ ህገመንግስቱ በቀጣይ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና ሴቶችን ማብቃትን የሚመለከቱ የተለያዩ የፖሊሲ እና የህግ ማሻሻያዎች ለውጥ ምክንያት ሆኗል፡፡ ህገመንግስቱን በመከተልም የሥርዓተ-ጾታ ዕኩልነትን እና የሴቶችን መብቶች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ህጎች በፌደራል እና በክልል ደረጃ ወጥተዋል፡፡ ከነዚህም የተሻሻለው የስራ ህግ፣ የሲቪል ሰርቪስ ህግ እና የቤተሰብ ህግ ይጠቀሳሉ፡፡

**የሴክተር ፖሊሲዎች:** በብሔራዊ ደረጃ ከወጡ ፖሊሲዎች እና ህጎች በተጨማሪ በሴክተሮች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ያለሙ የተለያዩ የሴክተር ፖሊሲዎች እና ደንቦች ተቀርጸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል እ.ኤ.አ በ1993 የወጣው የስነ-ህዝብ ፖሊሲ፣ የጤና ፖሊሲ፣ የ1994ቱ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ፣ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ፣ የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ ብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት የድርጊት መርሐ ግብር፣ የኢትዮጵያ ሴቶች በአጠቃላይ እና ለአርብቶ አደር ሴቶች በተለየ መልኩ የልማት እና የለውጥ ፓኬጅ እንዲሁም፣ ብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ፣ ብሔራዊ የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ፣ ብሔራዊ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እና ዕቅድ፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ስትራቴጂ፣ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን ጨምሮ የተለያዩ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊስካል ፖሊሲዎችን ያካትታል፡፡

ከነዚህ የሴክተር ፖሊሲዎች እና ስትራጂዎች በተጨማሪ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት ጉዳይ ብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት የድርጊት መርሀግብር፣ በፈጣን እና ቀጣይነት ያለው ልማት ድህነትን ማጥፋት በተሰኘው የአምስት ዓመት ዕቅድ እንዲሁም በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች እና አሁን ወደ ትግበራ የተገባው የአስር ዓመት የፐርስፔክቲቭ ዕቅድ ውስጥ ተካትቶ ታይቷል፡፡ ብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ የድርጊት መርሀግብር የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ከሚፈታባቸው መንገዶች መካከል የግብርና መሬት አቅርቦት፣ የስራ ዕድል ማስፋፋት፣ የግብርና ግብዓት እና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የተሻሻለ የእህል እና የእንስሳት ምርትን ማሳደግ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ የድርጊት መርሀግብር ውስጥ የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ለመፍታት ከተዘረዘሩ 12 የትኩረት መስኮች መካከል የተለዩ 7 መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ እንደሚሰራ ተቀምጧል፡፡ እነዚህም:-

- ድህነትን ማጥፋት እና ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ማብቃት
- የሴቶች እና ልጃገረዶች ትምህርት
- የስነ-ተዋልዶ መብት፣ ጤና እና ኤች አይ ቪ ኤድስን ማስቆም
- የሰብዓዊ መብት እና በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚፈፀም ጥቃትን ማስቆም
- በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሴቶችን ማብቃት
- ሴቶች እና አካባቢ
- የሴቶችን ጉዳይ ከመሰረቱ ለመለወጥ አስቸኳይ ተቋማዊ ሁኔታ

ተሳትፎ፣ ተጠያቂነት እና ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ምላሽ የሚሰጥ ተቋም:

- ◊ በፖለቲካ፣ በመንግስታዊ አሰራር እና ውሳኔ አስጣጥ ላይ የሴቶች ተሳትፎ
- ◊ ሴቶች እና ሚዲያ
- ◊ ሥርዓተ-ጾታን ከግምት ያስገባ በጀት

ነገር ግን እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች ሥርዓተ-ጾታን በመንግስት ፋይናንስ፣ በውጭ ሀብት ማሰባሰብ እና ማስተዳደር እንዲሁም በፊስካል ፖሊሲ ትግበራ ውስጥ አልታዩም፡፡ የፊስካል ፖሊሲ እና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደሮች በዲዛይን ወቅት የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ከግምት ያስገቡ ባይሆንም በተደረገ ማሻሻያ እንደ አዋጅ ያሉ ሰነዶች በተሻለ ደረጃ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን ከግምት ያስገባ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ የ2016ቱን

የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ በመጠቀም ሥርዓተ-ጾታን ከግምት ያስገባ በጀት በፕሮግራም በጀት ሂደት ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል። አዋጁ የሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሴክተሮች የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ በበጀት ዝግጅት ውስጥ ማካተት እንዳለባቸው ይጠቀሳል። ተቋሙ ስረዓተ ጾታን ከግምት ያስገባ የበጀት አሰራር መመሪያ ወደ ስራ ያሰገባ ሲሆን ይህም በሥርዓተ-ጾታ እና ሴቶችን የማብቃት ተግባር በብሔራዊ ዕቅድ እና በጀት ድልድል ውስጥ መካተቱን ለመከታተል ይረዳል፡፡ የመንግስት ስራ አስፈፃሚ አካላትን ተግባር እና ኃላፊነት የሚገልጸው አዋጅ ተቋማት የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ማካተት እንዳለባቸው ይጠቅሳል።

እንደ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት የሥርዓተ-ጾታ በጀት ተነሳሽነቶች (initiatives) ከሥርዓተ-ጾታ ጋር የተያያዙ ግቦች በፊስካል ፖሊሲ እና በአስተዳደር ውስጥ የሥርዓተ-ጾታን እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃትን ተግባር የማረጋገጫ መንገድ ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ አግባብ የኢትዮጵያ መንግስት የሥርዓተ-ጾታን ፅንሰ ሀሳብ እና በልማት ዕቅዶች ማካተትን እና ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ የሚሰጥ የበጀት አሰራር በሁሉም የሚኒስቴር መ/ቤቶች ለማካተት የተደረገው ጥረት መንግስት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት በመንግስት ፋይናንስ ውስጥ ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ የታየውን መሻሻል ያመለክታል፡፡ ሥርዓተ-ጾታን ከግንዛቤ ያስገባ የበጀት አሰራርን ለመደገፍ ተቋሙ የብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ እና በጀት መመሪያ በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች አሳትሟል።የውጭ ሀብት ማሰባሰብ እና ሥርዓተ-ጾታን በሚመለከት ተቋሙ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሴቶች ጉዳይ አጀንሲ ጋር በመተባበር ሰርዓተ-ጾታ እና የውጭ ድጋፍ ውጤታማነት የተሰኘ ማኑዋል አዘጋጅቷል።

## 3.3 ሥርዓተ-ጾታን በሚመለከት የተገቡ ቃል ኪዳኖች እና በአፈፃፀማቸው መካከል የሚታይ ክፍተት

ባለፉት ጥቂት አስርተ አመታት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መስክ ከማብቃት አንፃር በጉልህ የሚጠቀሱ የቃል ኪዳን ሰነዶች ተፈርመዋል። እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ባንክ በተዘጋጀ ሪፖርት መሰረት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ከማብቃት እንዲሁም የኢኮኖሚ አካታችነትን ዓላማ ያደረጉ 275 የሚሆኑ ማሻሻያዎች በ132 ሀገራት ተደርገዋል። ነገር ግን ውጤቶቹ በቅርበት በሚገመገምበት ወቅት በርከት ያሉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ፣ ቀጠናዊ እና ብሔራዊ የቃል ኪዳን ሰነዶች ቢፈረሙም በሥርዓተ-ጾታ ላይ የሚታየው አለመመጣጠን በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በርከት ያሉ በአለም አቀፍ፣ በቀጠና እና በብሔራዊ ደረጃ የተሰሩ ዳሰሳዎች እንደሚያሳዩት ሴቶች ከወንዶች ጋር በሚነፃፀሩበት ጊዜ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካው መስክ ዝቅ ያለ ተሳትፎ ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር አብዛኞቹ በብሔራዊ ደረጃ የተቀረጹ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ለሥርዓተ-ጾታ ትኩረት የማይሰጡ ወይም ሥርዓተ-ጾታን ከግምት ያላስገቡ ናቸው።

ዓለም አቀፉ የሥርዓተ-ጾታ (አለመጣጣም) ሪፖርት አራት መለኪዎችን በመጠቀም ሀገራት በሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ያሉበትን ደረጃ ያስቀምጣል። መለኪያዎቹም፡

- የኢኮኖሚ ተሳትፎ እና ዕድል
- ትምህርት
- ጤና እና በህይወት የመኖር ምጣኔ
- በፖለቲካ ብቁ መሆን ናቸው

በዚህም መሰረት የ2020ው ሪፖርት እንደሚያሳየው የሥርዓተ-ጾታ ክፍተት ወይም አለመመጣጠን ከአሁን ጀምሮ በሚቀጥሉት 99.5 ዓመታት ውስጥ አይቀየርም። ይህም ማለት ማናችንም ብዙዎች ልጆቻችንን ጨምሮ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በዕድሜያችን አናይም ማለት ይሆናል።

ይህንን ለመቅረፍ በተፈረሙ የቃል ኪዳን ሰነዶች እና በተገኙ ውጤቶች መካከል የሚታየውን ክፍተት ማጥበብ የትግበራ መንገዶችን መመልከት እንዲሁም ሊቀጥሉ የሚገባቸውን እና መቀየር ያለባቸውን ተግባራት ወይም አሰራሮች መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሴቶች በትምህርት፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካው እና በውሳኔ ሰጪነት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሻሻል ተጨማሪ ጥረቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ይህም እስካሁን የታዩ ቁርጠኝነቶችን ማጠናከር፣ በቁጥር በሚገለጹ ውጤቶች ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ሥርዓተ-ጾታን ያማከለ በጀት እና ዕቅድ፣ ውጤታማ የሆነ በውጤት ላይ የሚደረግ ክትትል እንዲሁም

ተቋማዊ ተጠያቂነት እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል።

በዚህም መሰረት በማክሮ ኢኮኖሚው ዘርፍ እና በገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን እና ኃላፊነት በርከት ያሉ የተቀረጹ እና በትግበራ ላይ ያሉ ፖሊሲዎች እና ሥርዓተ-ጾታን ከማካተት አንፃር ክፍተት ይታይባቸዋል። ለምሳሌ የፊስካል ፖሊሲ፣ የመንግስት እና የግል አጋርነት ፖሊሲ እንዲሁም የታክስ ስትራቴጂው ከዚህ አንፃር ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተመሳሳይ የተጠቀሱትን ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች የሚያስፈፅሙ የስራ ክፍሎች ስማርት ኢኮኖሚክስ የተሰኘውን መርህ የማይከተሉ ናቸው። በተጨማሪም የፌደራል በጀት ድልድል እና አስተዳደር የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ በበጀት መስሚያ ጊዜ ከሚናገሩት ባሻገር ሁሉም ሴክተሮች በበጀት ዝግጅት ወቅት የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ ከግምት ውስጥ ለማስገባት መስራት አለበት። በተያያዘም ኢትዮጵያ ሥርዓተ-ጾታን ያማከለ የበጀት መግለጫ ማዘጋጀት ላይ ልምምድ የሌላት በመሆኑ ለዚህም የሩዋንዳ እና የዩጋንዳ ተሞክሮ ሊወሰድ ይችላል፡ ፡ የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ በበጀት ውስጥ ማካተት ያለበት አካል ተግባሩን ለመፈፀም የሚያስችሉ መሰሪያዎች (ቱሎች) እና ሌሎች ግብዓቶች እጥረት ይታያል። በቅርቡ ወደ ተግባር የተሸጋገረው እና በተቋሙ የተዘጋጀው ዘመኑን የዋጀ ነው ተብሎ የሚታመንበት የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂ በራሱ በዘርፉ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን እና ሌሎች መሰል (cross cutting) ጉዳዮችን ከማገናዘብ አንፃር ምንም ያለው ነገር የለም።

# 04.

# የነባራዊ ሁኔታ ትንተና

## 4.1 ሀገራዊ ሁኔታ እና ዋና ዋና ሂደቶች-በሀገራዊ ደረጃ

ኢትዮጵያ በቀደመው ጊዜ ሴት የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ መሪ ያላት ቀዳሚ ሀገር ናት። ይሁን እንጂ ይህ አስደናቂ ታሪክ አሁን ያለውን ሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት እና አመራር ላይ ያላቸውን ሚና አያንፀባርቅም። ሴቶች እና ፍላጎቶቻቸው ለዘመናት ትኩረት አጥተው በመቆየታቸው ምክንያት ኢትዮጵያ ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ማግኘት ያለባትን ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት እና ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት የሚገኘውን ጥቅም ለማግኘት በ1995 ዓ.ም የተቀረጸው የሀገሪቱ ህገ መንግስት የሴቶችን እኩልነት የሚያረጋግጥ እና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ዓይነት መድሎ ስለማስወገድ የሚያትት አንቀጽ በውስጡ አካቷል። አሁን በስራ ላይ ያለው ህገመንግስት ለሴቶች እና ለወንዶች በሁሉም መስክ እኩል የስራ ዕድል፣ ሀብት የማግኘት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀም እንዲሁም የማስተላለፍ መብትን ጨምሮ ያጎናፅፋል። በተጨማሪም በ21ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ሴቶች አቅም ለመጠቀም የሚያግዙ የተለያዩ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሴቶች ፖሊሲ እና በህገመንግስት ደረጃ የሴቶች እና የወንዶች መብቶች እኩልነት ማረጋገጥ የሶስት አስርት አመታት ዕድሜ ብቻ ያለው ነው። አዋጅ ቁጥር 377/2003 ሴቶች በስራ ላይ የሚደርስባቸውን መድሎ በህገወጥነት ደንግጓል። በተጨማሪም የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 262/2002 ለሴቶች እና ለወንዶች እኩል የስራ እድል ማግኘትን ይደነግጋል። የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ እና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ያለ እድሜ ጋብቻ እና የቤት ውስጥ ጥቃትን እንዲሁም ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንደ ወንጀል ደንግጓል።

ህገመንግስቱም ሆነ ብሔራዊ ፖሊሲዎች በሥርዓተ-ጾታ ዙርያ ከተፈረሙ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች እና ኮንቬንሽኖች ጋር የተጣጣሙ ናቸው። ኢትዮጵያ በርከት ያሉ የሥርዓተ-ጾታ እና የሴቶችን እኩልነት የሚመለከቱ በሁሉም መልክ በሴቶች ላይ የሚደርሱ መድሎዎችን የማስቀረት ስምምነት (CEDAW)፣ The Beijing Platform for Action፣ የአፍሪካ የሰብዓዊ እና የህዝቦች ቻርተር ያሉ ዓለም አቀፍ እና ቀጠናዊ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖችን ብትፈርምም የሥርዓተ-ጾታ ችግር በሀገሪቱ በሁሉም መልክ ይስተዋላል።

በሀገሪቱ ላለፉት ሁለት አስርት ከተኩል ዓመታት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ማብቃት ተግባር የተሻለ ትኩረት አግኝቷል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ውስጥ የሚታየውን የሥርዓተ-ጾታ አለመጣጣም ለመፍታት ተሞክሯል። ይህም ሴቶች በካቢኔ ያላቸውን ድርሻ ወደ 50 በመቶ ከፍ በማድረግ የታየ ሲሆን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያላቸው መቀመጫ 38 በመቶ የታየ ቢሆንም በዝቅተኛ የፖለቲካ አደረጃጀት እና የአስተዳደር እርከን ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ምንም እንኳ እነዚህን የመሳሰሉ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ኢትዮጵያ የ2019 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሥርዓተ-ጾታ ኢንዴክስ ከ162 ሀገራት መካከል 125ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች።

የተለያዩ ጥረቶች በከፍተኛ አመራር፣ ባለበጀት ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና በፌደራል ደረጃ እየተደረጉ ይገኛል። ለምሳሌ ምንም እንኳ የስልጠናው ተጽዕኖ እና አተገባበሩ በፌደራል ደረጃ የተወሰነ ቢሆንም በሁሉም የፌደራል ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሥርዓተ-ጾታን ያማከለ በጀት አሰራር ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሁሉም የሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሥርዓተ-ጾታ የስራ ክፍሎች ቢኖሩም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሥርዓተ-ጾታን በሁሉም ደረጃ ማካተት በሚጠበቀው ደረጃ በዓመታዊ በጀት፣ ዕቅድ፣ ዕለታዊ የስራ ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ አልተከናወነም፡፡ በተጨማሪም መዋቀራዊ አደረጃጀት፣ በሰው ኃይል አደረጃጀት እና የስራ ቦታ የፖለቲካ ምህዳር በሴክተሮች መካከል ወጥነት መጉደል ይታይበታል፡፡ ይህም በየሴክተሩ የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ የስራ ክፍሎች የሴክተር ዕቅዶችን እና ሪፖርቶች በተገቢው ሁኔታ በመገምገም እና በመመዘን አስፈላጊውን ግብረ መልስ እና የወደፊት አቅጣጫ ማመላከቻ እንዳይሰጡ እክል ሆኖባቸዋል። በአብዛኞቹ መስሪያ ቤቶች መረጃ በፆታ በተከፋፈለ መልኩ እንዲቀመጥ አስገዳጅ ቢሆንም ይህ አልሆነም።

በሁሉም የባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በሚባል መልኩ የየመስሪያ ቤቶቹ ከፍተኛ አመራሮች ከሌሎች በተሻለ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በተመለከተ አጀንዳ የሚይዙ ቢሆንም አሁንም መሻሻል የሚችልበት ሁኔታ አለ። በሌላ በኩል የግንዛቤ ማነስ እና ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ያለመስጠት ችግር በመካከለኛ አመራሩ እና ከዚያ በታች ባሉ ሰራተኞች ላይ በስፋት ይታያል። እንደ ግብርና ሚኒስቴር ያሉ መ/ቤቶች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሥርዓተ-ጾታን ማካተት በመስሪያ ቤቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እና በጀት ውስጥ እንደ አንድ ምሰሶ(pillar) የተቀመጠበት ሁኔታ አለ፡

፡ የጤና፣ የግብርና እና የትምህርት ዘርፎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት፣ ሴቶችን ከማብቃት እና ሥርዓተ-ጾታን ከማካተት አንጻር የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሲሆኑ እንደ ንግድ እና ኢንዱስትሪ፣ የከተማ ስራ ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ያሉ ደግሞ ተስፋ የሚጣልባቸውን መሰረቶች የጣሉ ቢሆንም በሚጠበቀው ደረጃ ለመገኘት የቴክኒክ እና የሰው ኀይል እጥረት አለባቸው።

በአጠቃላይ ከቁልፍ ሰዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማየት እንደተቻለው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት፣ ማካተት እና ትግበራውን በተመለከተ በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያዎቹ ሴክተሮች እንደ ጤና፣ ትምህርት እና ግብርና (በዚህ ሰነድ ውስጥ ከዚህ በኋላ ባለተስፋ ሴክተሮች ተብለው የሚጠሩ) ግልፅ የሆነ የስርዓተ-ፆተ አሰራር በእቅዶቻቸው፣ በሪፖርቶቻቸው እና በበጀቶቻቸው ውስጥ ያካተቱ ናቸው። ነገር ግን ተጠሪነታቸው ለነዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሆኑ ተቋማት ደረጃ ከነዚህ መስሪያ ቤቶች በታች እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ባለተስፋ ሴክተሮች በራሳቸው የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን ወደ ንዑስ ዘርፎች ወስዶ ከመተግበር አንጻር ችግሮች ይታዩባቸዋል። በነዚህ ሴክተሮች በቂ በጀት ቢኖርም ችግሮች የሚመነጩት ስራዎች የሚሰሩት የችግሮችን ምንጭ እና ችግሩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን የመለየት ተግባር በበቂ የመነሻ ጥናት ታግዞ ባለመሆኑ ነው። በተጨማሪም ሴክተሮቹ አንዳንድ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ የትኩረት ማነስ ችግርም ይታይባቸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጡት ሴክተሮች በሥርዓተ-ጾታ እና ሴቶችን ከማብቃት አንጻር ወደ ፊት እየመጡ የሚገኙ እና የተለያዩ ለውጦችን በማድረግ ላይ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ በሴክተር እና በተቋም ደረጃ የሥርዓተ-ጾታን ጉዳይ የማካተቻ ስትራቴጂ የቀረጹ እና የትግበራ መመሪያ ያዘጋጁ ሲሆኑ የሰው ኃይልን ጨምሮ የቴክኒክ አቅም ክፍተት የሚታይባቸው ናቸው።

በሶስተኛት ደረጃ ላይ የሚቀመጡት ሴክተሮች (በዚህ ሰነድ ውስጥ ከዚህ በኋላ ዝቅተኛ ፈፃሚዎች ተብለው የሚጠቀሱ) አብዛኞቹን ሴክተሮች የሚያጠቃልሉ ሲሆን ምንም ዓይነት የሥርዓተ-ጾታ መተግበሪያ ማዕቀፍ፣ የትግበራ ዕቅድ፣ በጀት እንዲሁም ሌሎች ለትግበራ የሚረዱ መሳሪያዎች የሌላቸው እና በሀገር ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረሰባቸውን ስምምነቶች ለማስፈፀም ዝግጁ ያልሆኑ እዲሁም የሥርዓተ-ጾታ ዳሬክቶሬትን ጨምሮ በተዋረድም ሆነ በጎንዮሽ ከሚገኙ ተቋማት ጋር ጉዳዩን በሚመለከት የስራ ግንኙነት የሌላቸውን ይይዛል። እነዚህ ሴክተሮች ያላቸው የሰው ኃይል አቅም፣ ሙያ እና ሀብት ጉዳዩን ለመፈፀም በቂ ካለመሆኑ በተጨማሪ የበጀት እጥረት እንዳለባቸው ይገልፃሉ። በአጠቃላይ በነዚህ ሴክተሮች የክትትል እና ግምገማ ተግባርን ማከናወን የተለመደ አይደለም። በመሆኑም ሴክተሮቹ የድህረ ትግበራ ምዘና ለማድረግ አስቸኳይ ሁኔታዎች የላቸውም፡ ፡ በሴክተሮች የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ሪፎርም ሂደት ፋይናንስ የማድረግ ሂደት በፋይናንስ የማድረጊያ ተቋማትም ሆነ በሶስቱም ደረጃዎች በሚገኙ የአስፈፃሚ ተቋማት ተግባራዊነት ውስን ነው። ይህም ተቋማዊ አደረጃጀት ከፌደራል፣ ክልል፣ ዞን እና ወረዳዎች በአግባቡ በተዋረድ የተዋቀሩ ባለመሆኑ ነው። በፌደራል እና ከክልል በታች ባሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች መካከል ከሚታይባቸው ልዩነቶች አንዱ የበጀት አስተዳደር ሲሆን ይህም ለምሳሌ በፌደራል የፕሮግራም በጀት ተግባራዊ ሲደረግ ከክልል በታች ባሉ መዋቅሮች የዝርዝር የወጪ አርዕስት የበጀት (Line Item budget) አሰራርን በተግባር ላይ እየዋለ መገኘቱ ነው። በተመሳሳይ በፕሮግራም በጀት ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ከማብቃት አንፃር በሁሉም ፕሮግራሞች ቅንጅት አለመኖር፣ ለሥርዓተ-ጾታ እና ሴቶችን ለማብቃት የታለመ ዋና (ኮር) በጀት አለመኖር ከሌሎች እንደ የአቅም ማነስ እና ትኩረት ያለመስጠት ችግሮች ጋር ተዳምሮ እየታየ ላለው ውስን የሥርዓተ-ጾታ፣ ሴቶችን የማብቃት አጀንዳ እና ለጉዳዩ ትኩረት የማይሰጥ የበጀት አሰራር መንስኤ ሆኗል።

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሥርዓተ-ጾታን ማካተት በሚመለከት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች የተደረገው ዳሰሳ የሚከተሉትን የአሰራር ማነቆዎች ለይቶ አውጥቷል።

- የገንዘብ ሚኒስቴርን ጨምሮ በርካታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሥርዓተ-ጾታ ኦዲት ያላከናወኑ እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ከማብቃት አንፃር ያሉበትን ደረጃ ያልዳሰሱ መሆናቸው፣
- የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር ከአደረጃጀት፣ ከትግበራ እና ከክትትል አንፃር የሚታይ ድክመት፣

- ሴቶችን በኢኮኖሚ ከማብቃት እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ከማስፈን አንፃር ቅድሚያ ያለመስጠት፣

- የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በአግባቡ የተደራጀ የትግበራ ዕቅድ፣ የአቅም ውስንነት እና ለጉዳዩ ትኩረት ያለመስጠት ችግር በሚታይበት በኢኮኖሚ ሴክተር ከፍ ለማድረግ የሚያስችል የስርዓት እና ለጉዳዩ ግንባር ቀደም ተቋም (Entry Point) ልየታ ላይ የሚታይ ችግር፡፡

- የፖሊሲ እና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች

  ◊ በመንግስት ፋይናንስ እና የፊስካል ፖሊሲ አሰራር ውስጥ በግልፅ የተለየ የሪፎርም ጥቆማ አለመኖር፣

  ◊ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም በተለይም የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም በሴቶች እና በወንዶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በግልፅ ያልተቀረፀ እና ያልተገመገመ መሆኑ፡፡ በተመሳሳይም እንደነዚህ ዓይነት ግምገማዎች ለህዝብ የሚደርሱበት ሁኔታ መኖር እና ይህም በዘርፉ የሚፈለገውን የማህበራዊ ለውጥ እንዳይመጣ እንቅፋት ሆኗል፣

  ◊ በብሔራዊ የፊስካል ፖሊሲ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታጉዳይ ለብቻው ተለይቶ በክፍል አለመቀመጡ፣

  ◊ የሥርዓተ-ጾታን ከግምት ያስገባ በጀት በፕሮግራም በጀት ውስጥ በተገቢው መልኩ ያልተዋሃደ እና የሴቶችን ፍላጎቶች በፕሮግራም በጀት ውስጥ በተቀላጠፈ መልኩ ለመተግበር እና ለማረጋገጥ በሚያግዝ መልኩ አለመቀመጡ፡፡

- ሀብት ማስተዳደር እና ምደባ

  ◊ በጾታ የተከፋፈለ መረጃ አለመኖር፣

  ◊ ከትግበራ በፊት የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና እና የመነሻ ጥናት አለማድረግ፣

  ◊ የታክስ፣ የፊስካል ፖሊሲ እና የውጭ ሀብት ዘርፎች በሀገር ደረጃ ለሚደረገው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን ከማብቃት እንቅስቃሴ ያላቸውን ሚና በሚመለከት የፖሊሲ ጥናት አለመኖር፣

  ◊ በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች የሥርዓተ-ጾታ ኦዲትን በሚመለከት መረጃ እና ጥናት አለመኖር፡፡

## 4.2 የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን በሚመለከት የገንዘብ ሚኒስቴር ያለበት ሁኔታ

የሴቶችን ጉዳይ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ከማሻር አንፃር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁለት ሚናዎች ሲኖሩት አንደኛው በውስጥ የሴት ባልደረቦችን አቅም በማሳደግ እንዲሁም ለብቁ ባለሙያነት እና አመራር ሰጪነት ደረጃ በማብቃት በሀገር ደረጃ ጥራት ያለው የሲቪል ሰርቪስን የማፍራት ውጥን አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ብሄራዊ በጀት የማዘጋጀት፣ የፊስካል እና የውጭ ሀብት ፖሊሲዎችን የመቅረፅ፣ የውጭ ሀብት በዕርዳታ እና በብድር መልክ የማሰባሰብ እና የማስተዳደር፣ የመንግስት ፋይናንስን በበላይነት የመቆጣጠር እና የመንግስት ተቋማት ላይ የውስጥ ኦዲት የማድረግ እና የመሰሰሉትን በአዋጅ ስልጣን የተሠጠው ተቋም ነው፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመንግስታት፣ ቀጠናዊ እና ብዙ ሀገራት የሚሳተፉበት ዓለም አቀፍ ትብብሮችን የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚፈጥሩ ከዓለም አቀፍ እና ቀጠናዊ ተቋማት ጋር በመተባበር ይመራል፡፡ አሁን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ዘንድ የሚታየው ሁኔታ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና ሴቶችን የማብቃት ስራን ለመከወን የሚያግዝ ነው፡፡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኘው የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት እና ባለሙያዎች እንደ በጎ የሚታዩ ቢሆንም የስራተኞች ዝውውር ይህንን ስትራቴጂ ከመተግበር አንፃር ተግዳሮት እንደሚሆን ይታመናል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ዘርፍን እደሚዘውር ተቋም ከመሆኑ አንፃር ከሥርዓተ-ጾታ ማካተት እና ሴቶችን ከማብቃት አንፃር በሚጠበቀው ደረጃ አይደለም፡፡

የሥርዓተ-ጾታእኩልነት ጉዳይ በፊስካል ፖሊሲ ውስጥ ወደ መሬት ያልወረደ ሲሆን በሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ላይ ከተደረገው የቀረጥ ነፃ ፍቃድ ውጪ ተጨባጭ የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች በመስሪያ ቤቱ በሚገኙ የስራ ክፍሎች ውስጥ እና በሴክተር መስሪያ ቤቶች በጀት ውስጥ መካተቱን እና የሚወስዱትን እርምጃዎችን የመከታተያ መንገዶችን የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተግባራት ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ምላሽ ከመስጠት አንፃር አዝጋሚ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ሲሆን አፈፃፀሙም በጉዳዩ ለሌሎች ተቋማት አርአያ

እንዲሆን ከሚጠበቅ ተቋም በሚጠበቅበት ደረጃ አይደለም። በተቋሙ ትኩረት የሚሹ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን በስራ ክፍሎች በጀት እና ዕቅድ ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች ለመከታተል፣ ለመገምገም እና ግብረ መልስ ለመለዋወጥ የሚያስችል መድረክ የለም።

የገንዘብ ሚኒስቴር በፊስካል ፖሊሲ በኩል ሴቶችን በኢኮኖሚ የማብቃት ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በተቋሙ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ጉዳይን በቁልፍ የልማት እንቅስቃሴዎች፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ የስራ ፈጠራ እና ገንዘብ አቅርቦት አንጻር በሥርዓተ-ጾታ ደረጃ የሚታየውን አለመመጣጠን ለመፍታት ከፍተኛ የሆነ የተነሳሽነት ችግር ይታያል። ከዚህም በተጨማሪም ተቋሙ በስራ ክፍሎች ውስጥ እና መካከል በስርዓተ-ጾታ ጉዳይ የላቀ አፈፃፀም ያሳዩ ባልደረቦችን የሚያበረታታበት አሰራር አልዘረጋም።

በባለሙያ ደረጃ የሰራተኞች ተዋፅኦ ከስረዓተ ጾታ ዕኩልነት አንፃር የተመጣጠነ ነው ቢባልም በውሳኔ ሰጪነት ደረጃ ወይም በከፍተኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ የሚባል ነው። ይህም ተቋሙ ትኩረት የሚሹ የስረዓተ ጾታ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ለዘብተኝነት እንዲያሳይ እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማሻገር የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ለመተግበር እክል ይፈጥርበታል።

# 05.


## ትንተና

## 5.1 ጥንካሬ፣ ድክመት፣መልካም አጋጣሚ፣ ስጋት እና የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ ትንተና

የውስጥ እና የውጭ (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የቴክኖሎጂ፣ አካባቢያዊ እና የህግ) ምክንያቶች ጥልቅ ትንተና ገንዘብ ሚኒስቴር ጥንካሬዎችን እና ድክመቶችን በሚገባ እንዲረዳ እና እንዲያውቅ ያስችለዋል። እንደዚሁም እንደዚህ ዓይነቱ ትንታኔ ለእድገትና ለልማት እምቅ አቅም ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመለየት ወይም በጥልቀት ሊገመገሙ የሚገባቸውን ጉዳዮች በመለየት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስልትን በውጤታማነት እና በብቃት ለማስፈፀም ጥንካሬን እና ዕድሎችን በመጠቀም ላይ በማተኮር ድክመቶችን እና ስጋቶችን ለመቅረፍ ይረዳል። ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሁን ባለው የገንዘብ ሚኒስቴር የሥራ እንቅስቃሴ በተለይም በሥርአተ-ጾታ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ላይ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የተዳሰሱ ሲሆን መልካም ዕድሎች እና ተግዳሮቶችን በተመለከተ ደግሞ ከገንዘብ ከሚኒስቴር ባሻገር መስሪያ ቤቱ ወይም የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከተቀረው አለም ጋር በፖለቲካ እና ማህበራዊ ግንኙነቶች በተመለከተ ከአጠቃላይ አስቻይ የስራ አካባቢ ተዳሰዋል። ከሚመለከታቸው ዋና መረጃ ሰጭ አካላት ጋር ጥልቅ ምልከታ እና ምክር ከተደረገ በኋላ የሚከተሉት ጉዳዮች/ዘርፎች በሁኔታ ትንተናው ወቅት ተለይተዋል-

### ጥንካሬ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአገሪቱ ሁሉን አቀፍ የፋይናንስ ልማት እውን ማድረግ የሚያስችለው መሠረታዊ ምሰሶዎች አሉት። መልካም የሥራ ግንኙነት እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሻለ የአደረጃጀት መዋቅር፣ የሥርአተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጠንካራና የተቀናጀ የሥራ ባህል የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥንካሬዎች ማሳያ ነው። አሁን ያለው ሀገራዊው ሥርአተ-ጾታን ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እና የዘርፉ ተመሳሳይ ፍላጎቶች በተመጣጠነ ሁኔታ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በማስጠበቅ ከፍተኛ የልማት ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል። በተጓዳኝ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራር አዎንታዊ የሥራ ሁኔታ እና ድጋፍ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ልማትና ትግበራ አጀንዳ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የበለጠ አምጥቶ ለመጠቀም የሚያስችል ቁልፍ ጠንካራ ጎን ነው። በተጨማሪም የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ በቀላሉ ለማዋሃድ ቀላል ይሆናል ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በሥርአተ-ጾታ መነፅር ተግባራቸውን ለመፈፀም በሀሳብ ደረጃ ቀና በመሆናቸው። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ሠራተኞችና ማኔጅመንቱ ቁርጠኝነት የተሻለ መግቢያ ነጥብ ነው ከተጨማሪ የሰራተኛ ቅጥር ፍላጎት ባሻገር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ-ጾታ ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ በሚደረጉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ውስጥ ዳይሬክቶሬቱ የራሱን ድርሻ ይወስዳል። በተጨማሪም በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ የተቋቋመው የክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በመዋቅሩ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ዩኒት ማካተቱ ተግባሪዊ ለማድረግ የተዘጋጀውን ስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥንካሬ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል አመላካች ነው።




## ድክመት

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወደ ራሱ ውስጥ ሲመለከት መሻሻል ያለባቸውን ዋና ዋና ድክመቶችና ክፍተቶችን በመለየት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለማረጋገጥ ተመራጭ አካሄድ ነው።


በዚህ መሠረት በጀት አመዳደብ ከሥርዓተ-ጾታ አንፃር የተመደበ ስለመሆኑ እንዲሁም የተመደበው በጀት በትክክል የሥርአተ ጾታን እኩልነትን ለማረጋገጥ ስለመተግበሩ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል አሰራር አለመኖር በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የታየ ቁልፍ ክፍተት ነው። በተመሳሳይ በውሳኔ ሰጪዎች እና የቴክኒክ ባለሙያዎች የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን (GRB) ተግባራዊ የማድረግ ሙሉ ኃላፊነት አለመውሰድና እና የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖሩ በሁኔታው ትንተና የተለየው ሌላው ቁልፍ ክፍተት ነው።

በተጨማሪ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማንዴት የሥርዓተ-ጾታ ከሌሎች የሥርአተ-ጾታ የሥራ ክፍል ጋር በዕቅድ፣ በበጀት፣ በክትትልና ግምገማ ቅንጅት ባለመኖሩ ሴቶችን በማብቃት ሂደት የተገኙ ውጤቶችን የተበጣጠሱ እና አመርቂ ውጤት ያልታየባቸው መሆኑ ትልቅ የታየ ድክመት ነው፡፡ ለምሳሌ በገንዘብ ሚኒስቴር የሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት እና በሌሎች መስሪያ ቤቶች ተመሳሳይ ዳይሬክቶሬቶች በጣም ውስን የሆነ መስተጋብር ነው ያላቸው። በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ጉልህ የሆነ የክህሎት ክፍተት (ማለትም የሥርዓተ-ጾታ ባለሙያዎች) በሰፊው ይታያል። ይህም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሌሎች ሚኒስቴር መስሪያቤቶች በአመት አንድ ጊዜ የ ሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ስልጠናን ከመስጠት የዘለለ ድጋፍ የማድረግ አቅም እንዳይኖረው አድርጎታል። ይህም የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ከመደበኛ እቅድ እና ትግበራ አንጻር ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል።

በሌላ በኩል የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ከዚያ ባሻገር ለፖለቲካ ዓላማ ብቻ ነው እየዋለ ያለው። የሥርአተ ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ሴቶችንና ወንዶችን በልማት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ወሳኝ ለውጥ ለማምጣት በሰው ሀይልም ሆነ በካፒታል በሚገባ የተደራጀ አይደለም።

በ SWOT ትንተና ወቅት የተለዩት ሌሎች ቁልፍ ክፍተቶች የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ሥርዓተ-ፆታን ለማቀናጀት ያላቸው ቁርጠኝነት ደካማ መሆኑ ነው። የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት የአቅም ግንባታ ስልጠናም የበጀት ስርዓቱን በተለይም የፕሮግራም በጀት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭ እንዲሆን ለማድረግ ባለው አቅም ላይ ውስንነት አለበት። ይህም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ እና ራሱን የቻለ የሥርአተ-ጾታ ፕሮጀክት ለመንደፍ እንዳይችል አድርጎታል፡ ፡ በዚህ ላይ በሁኔታዎች ላይ የተደረገው ትንታኔ እንደሚያሳየው በሥርዓተ-ፆታ እና በጾታ የተከፋፈሉ መረጃዎች እጥረት እንዳለ ሆኖ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዕቅድን ለማዘጋጀት የግንዛቤ፣ የእውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ችግር መኖር ሴቶችን ለማብቃት እና እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋና ድክመት ሆኖ ተገኝቷል፡ ፡


በሌላ በኩል የሥርዓተ-ጾታ ባለሙያዎች በተገቢው ቦታ አለመገኘታቸው በእያንዳንዱ ክፍል የሚነሱ ሥርዓተ-ፆታዊ ጉዳዮችን እና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚያነሳቸው ማሻሻያዎች ተቀባይነትን ይቀንሰዋል። በዕለት ተዕለት የሥራ ልምዶች የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳዎችን በማቀናጀት ለመስራት ቁርጠኝነት አለመኖር እና ሴቶችን ለማብቃት የሚያግዙ አማራጮችን ለመፈለግ ተነሳሽነት አለመኖር ክፍተቶች ይስተዋላል።



## መልካም አጋጣሚዎች

የኢትዮጵያ መንግስት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን ጠንካራ የፖለቲካ እና ተቋማዊ ቁርጠኝነት እንዳለው አረጋግጧል። ለዚህም ማሳያ የሀገሪቱ ህገ-መንግስት በወንድ እና በሴት መካከል እኩል መብትን በማወጅ በሥርዓተ-ፆታ ወይም በጾታ ላይ የሚደረግ አድልዎ ሁሉ ኢ-ፍትሃዊ እንደሆነ ተቀምጧል። በአገር አቀፍ ደረጃ የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን የሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት / መምሪያ በሁሉም የመንግስት ተቀማት ውስጥ ይገኛል። ይህም ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ የመንግሥት መዋቅሮች ሁሉ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ በጀትን ለማረጋገጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትልቅ መሳሪያ ነው። ከአገራዊ ምቹ አሰቻይ ሁኔታ (enabling environment) በተጨማሪ ኢትዮጵያ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፍ የሥርዓተ-ጾታ ስምምነቶችና ማዕቀፎች ያሳየችው ቁርጠኝነት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጥምረት እንዲፈጥር እና በአገሪቱ የሴቶች ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ያስችለዋል።


ከገንዘብ ሚኒስቴር ተልዕኮ አንዱ የውጭ ሀብትን ማሰባሰብ ሲሆን ሴቶችን ለማብቃት እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚቀረጹ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ በልማት አጋሮች በኩል ተገቢው ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። ለዚህም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈጠራ የታከለበት እና ኢኮኖሚያዊ የሆነ ፕሮጀክት ቢቀርፅ የበለጠ ሀብት ወደ ሀገር እንዲፈስ በማድረግ፣ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ማጎልበት እና ሴቶችን ማብቃት ያስችላል። በተጨማሪም አገሪቱ ያወጣቻቸው የሕግ ማዕቀፎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ እጅግ ምቹ ናቸው። የተግባራዊ ሴቶች መር የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት እና የውይይት መድረኮች መኖር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከእነዚህ አካላት ጋር በመተባበር ሴቶች እና ወንዶችን ያለ አድልዎ ተጠቃሚ የሚያደርግ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ልማት ለማሳካት እጅግ ጠቃሚ ናቸው።



## ስጋቶች

በኢትዮጵያ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እንዲረጋገጥ መልካም ዕድሎች ቢኖሩም በተቃራኒው በርካታ አሉታዊ ምክንያቶችም አሉ። እንደ ማንኛውም ታዳጊ አገር በተቋማዊ የአስተዳደር ማዕቀፎች ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን እውን ለማድረግ የዘርፍ እና አገራዊ ቀጣይነት ያለው የፖለቲካ ቁርጠኝነት የለም። በግል እና በዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ያለው በተደጋጋሚ የሚቀያየር የአስተዳደር መዋቅር፣ በጣም ከፍተኛ የደመወዝ ልዩነት የመንግስት አካላት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ውጤታማነት ትግበራ ላይ የሚያደርጉትን ጥረት በመግታት ከፍተኛ ስጋት ይሆናል።

በሌላ በኩል የሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት በግል ተቋማት ውስጥ አለመገኘት ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት እና ለሌሎች ትግበራዎች ተጨማሪ የመዋቅር አለመጣጣም ይፈጥራል። ሆኖም የሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት በሁሉም የመንግስት ተቋዋማት ውስጥ ቢኖርም፣ የተቋዋሙ መዋቅር እና የተሰጠው ተልእኮ በሁሉም ዘርፎች የማይጣጣሙ ናቸው ። በዘርፉ ባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ለሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት የሚመደብ በጀት አለመኖር ሌላው በጾታ እኩልነት እና እኩልነትን ለማጎልበት የሚደረጉ ክንውኖችን ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ ተግዳሮት ነው። በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳዎችን በማቀድ እና ማስፈጸም አኳያ ሰፊ ክፍተት ይስተዋላል። እንደዚሁም ሥርዓተ-ጾታን እና የመንግስት ፋይናንስን፣ የጾታ እና የፊስካል ፖሊሲን፣ የሥርዓተ-ጾታ እና የውጭ ሀብት ማሰባሰብን አስመልክቶ ከመንግስት ተቋማት እና ከልማት አጋሮች ጋር ለመወያየት የሚያስችል የተደገፈ እና የተደራጀ የውይይት መድረክ አለመኖሩ ፍጥነት ባለው መልኩ ተሻሽሎ ወደ ዕድል ካልተለወጠ በስተቀር እንደ ስጋት ሊያገለግል ይችላል።




ስለሆነም ከላይ የተገለጹት ግኝቶች እና በ SWOT ትንተናው የተለዩት ሌሎች ቁልፍ ጉዳዮች በበጀት፣ በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በውጭ ሀብት ማሰባሰብ እና በመንግሥት ፋይናንስ ጎራዎች ውስጥ ለጾታ እኩልነት ቁልፍ ስትራቴጂ እንደ መነሻ ያገለግላል።

## 5.2 የባለድርሻ አካላት ትንተና

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና የትኩረት አቅጣጫ አጀንዳ ከግለሰብ እስከ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ተዋንያን ደረጃ ያሉ ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረትና ትብብር ውጪ እውን አይሆንም። በሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ውስጥ የባለድርሻ አካላትን ሁሉን አቀፍ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎን ማሳደግ እና ማረጋገጥ ውጤታማ አሰራርን በእጅጉ ይደግፋል፡ ፡ በተጨማሪም ከገንዘብ እና ከግለሰብ ወይም ከድርጅት ሚኒስቴር ጋር አብረው የሚሰሩ የሴቶችና የወንዶች ባለድርሻ አካላት በገንዘብ ሚኒስቴር ተልእኮ እና አተገባበር እርምጃዎች ፣ በሀብት አመዳደብ ላይ በሚሰጡት ቅድሚያዎች እና አመለካከቶች ልዩነት ሊጎዱ እንደሚችሉ መዘንጋት የለበትም ። ስለሆነም የባለድርሻ አካላት የሥርዓተ-ጾታ ሚዛናዊ ምክክርን ማረጋገጥ በአሁኑ ጊዜ ለሚገጥሟቸው ቅድመ-ተለይተው የሚታዩ ክፍተቶች እና ችግሮች ሊኖሩ የሚችሉ መፍትሄዎችን ለመለየት እና መጪውን ጣልቃ ገብነት ለመገምገም ያስችላቸዋል።

የበርካታ ግንኙነቶች ባለድርሻ አካላት በሚፈለገው ደረጃ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በሁሉም ደረጃ ለማምጣት በጋራ ሊሰሩ ይችላሉ ። ባለድርሻ አካላት ከጥቃቅን-ደረጃ (የግለሰብ እና የአከባቢ ተዋናዮች) ፣ ሜሶ-ደረጃ (የክልል ተዋንያን) እና ማክሮ ደረጃ (ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ተዋንያን) እንደየደረጃቸው ፍላጎት እና የሥርዓተ-ጾታ አጀንዳ ላይ ተመስርተው ይመደባሉ።




ምስል 1- የሥርዓተ-ጾታ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት-ተጽዕኖ ማትሪክስ

የባለድርሻ አካላትን ፍላጎትና ተጽዕኖ መሠረት በማድረግ ባለድርሻ አካላትን በአምስት ምድብ ማለትም የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ቁልፍ፣ ውስጣዊና የውጭ ባለድርሻ አካላት ተሰኝተው ተመድበዋል፡ ፡ የመጀመሪያ ደረጃ ባለድርሻ አካላት በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ በቀጥታ ተጽዕኖ የሚደረጉ ባለድርሻ አካላት ሲሆኑ (ለምሳሌ በገንዘብ ሚኒስቴር ፋይናንስ በሚደረግ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ሴቶች፣ የበጀት አካላት፣ ሴት የሥራ ፈጣሪዎች እና የሴቶች ድርጅቶች (ኢንተርፕራይዞች)፣ በሌላ በኩል በሁለተኛ ደረጃነት ባለድርሻ አካላት ሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የሚደረጉ ናቸው፡፡

ቁልፍ ባለድርሻ አካላት እነዚህ የስትራቴጂው ትግበራ ማዕከል ተዋንያን የሆኑ ባለድርሻ አካላት ናቸው። በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት በስትራቴጂው አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እና ተጽዕኖ አላቸው። የእነዚህ ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች ለስትራቴጂው ትግበራ ወሳኝ ናቸው (እነዚህም የገንዘብ ሚኒስቴር ፖሊሲዎች ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው ሴቶች፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች) ምክንያቱም እነዚህ ቁልፍ ተዋናዮች በመሆናቸው። በተጨማሪም የስትራቴጂው አፈፃፀም ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ከፍተኛ (አዎንታዊ / አሉታዊ) ተፅእኖ ያላቸው ባለድርሻ አካላትም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂን ለማሳካት ቁልፍ ተዋናዮች ናቸው። በስትራቴጂው ተግባራዊነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ባለድርሻ አካላት መንግስትን፣ የልማት አጋሮችን፣ ለጋሾችን፣ ማህበረሰብን ወዘተ ያካትታሉ።


በተመሳሳይ የስትራቴጂው አፈፃፀም ላይ የውስጥ እና የውጭ ባለድርሻ አካላት ጉልህ የሆነ ተፅእኖ አላቸው። በመሆኑም የውስጥ ባለድርሻ አካላት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ሴት እና ወንድ ሰራተኞች፣ የሥራ ክፍሎች እና ዳይሬክቶሬቶች፣ ንዑስ ክፍሎች እና ቢሮዎችን ያጠቃለለ ይሆናል። የውጭ ተዋንያን በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ተጠቃሚ የሆኑና የገንዘብ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር አካል ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ናቸው። የውጭ ባለድርሻ አካላት የሚያካትታቸው የሲቪክ ማህበረሰብ አደረጃጀቶችን፣ የፌደራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እና የበለበጀት መስሪያ ቤትችን፣ ኩባንያዎችን፣ የቴክኒክ ባለሙያዎችን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና አቅጣጫ ጠቆሚዎች (think tanks) ወዘተ።

ከላይ የተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዩች ዳሬክቶሬትን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ ትግበራ ጉልህ ስኬት የማስገኘት አቅም አለው። ከዘርፉ ቁልፍ እና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የህግ እና የቴክኖሎጂ ዘርፎች ጋር ጥምረት መፍጠር ለተሻለ የስትራቴጂው ቁልፍ ግብዓቶች ይሆናል።

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ንድፍ አጠቃላይ ዓላማ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ ደህንነትን የሚያረጋግጥ ሁሉን አቀፍ ልማት ማረጋገጥ ነው። ስለዚህ የስትራቴጂው አተገባበር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶችን በዘላቂነት በሚፈታ መልኩ መቀረጽ አለበት። ለዚህም የገንዘብ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት/ አጋሮች ጋር በተለይም በሴቶች ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ እና የህግ ችግሮች ላይ ስልታዊ ጥምረት መፍጠር አለባቸው።

ገንዘብ ሚኒስቴር የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ እና ለሴቶች የስራ እድሎችን ለማስፋፋት ቀዳሚነት ከሚወስዱ የኢኮኖሚ ዘርፎች እና ተዋንያን (እንደ ግብርና ሚኒስቴር ፣ የከተማ ሥራ ፈጠራ ኤጄንሲ ፣ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ፣ የፋይናንስ ተቋማት ወዘተ) ጋር ጥምረት ለመፍጠር አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ስለሆነም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማጎልበት እና በሴቶች ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነት እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ላይ አሁን ያለበትን አስከፊ ሁኔታ ለማሻሻል ሚኒስቴሩ ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች እና ከግለሰብ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር አብሮ መሥራት ይኖርበታል።

የህብረተሰቡ ማህበራዊ ደህንነት ካልተጠበቀ እና በግልጽ እስካልተረጋገጠ ድረስ የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማሳካት አይቻልም። ስለሆነም በማኅበራዊ ልማት ላይ የሚሰሩ በርካታ ተዋንያን ተባብረው ለተሻለ የሥርዓተ-ፆታ-ለውጥ እንቅስቃሴ ጥምረት መፍጠር ያስፈልጋል። ገንዘብ ሚኒስቴር ከሌሎች ድርጅቶች ፣ ቡድኖች እና ግለሰቦች ጋር በመተባበር አጠቃላይና መጠነ ሰፊ ሥርዓት፣ ማህበራዊ-ሁሉን አቀፍ ልማት ለማረጋገጥ ጠንካራ አጋርነት መፍጠር አለበት። በጤና ፣ በትምህርት ፣ በሰላም (inter and intra-group reconciliation) እና የመሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ለመተባበርና ለመሰተፍ ቁልፍ አጋሮች በመሆናቸው በኢኮኖሚም ሆነ ማህበራዊ መልክ ትስስሩ እንዲቀጥል በሂደት በሕጋዊ ጥምረት መደገፍ አለባቸው። ስለሆነም የገንዘብ ሚኒስቴር በሕግ ማስከበር ላይ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት (ተቋማት ፣ ማኅበራትና የሕግ ባለሙያዎች) ጋር ስትራቴጂያዊ አጋርነትን መፍጠር አለበት።




አሁን ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚያመለክቱት በሥርዓተ-ጾታ መካከል ያለው ልዩነት እና ጾታዊ ትንኮሳ በሁሉም ቦታ የሚፈጸም እና ዘላቂ የልማት አጀንዳዎችን የሚፈታተን ጉዳይ ነው። በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጂ በአለም ላይ የልማት አጀንዳዎችን ለማሳደግ እና የጾታ ልዩነትን ለመቀነስ እንደ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በሴቶች ላይ ያለውን ጫና ለማቃለል እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ በቴክኖሎጂ ልማትና ስርጭት ላይ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት ወሳኝ ጊዜ አሁን ነው፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር በቴክኖሎጂ ዘርፍ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራቱ በሁሉም የሥርአተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት አመዳደብ እቅድ እና ትግበራን ለመከታተል ይረዳዋል። በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ጥምረት መፈጠር ለሴቶች የሥራ ዕድል፣ የሥራ ፈጠራ ክህሎት፣ የቢዝነስ ልማት መስክ አተገባበር እና ሌሎችንም በጉልህ ያሻሽላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የቴክኖሎጂ ጥምረት በሥራ ቦታ ላይ የሚከሰቱ ጾታዊ ትንኮሳን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ፣ ለመጠበቅ እና ለመፍታት እንደ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

የሀገሪቱ የበጀት ስርዓት ላይ የተለዩት ቁልፍ ክፍተቶች የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን እና የሴቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ትራንስፎርሜሽን ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት የሁሉም በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚሰሩ አካላት ጥምረት ለፌዴራል እና ለክልል የመንግሥት አካላት በዕቅድ የተላለፈ እና የፈሰሰ በጀት ሁሉ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ያስፈልጋል ፡፡ በተጨማሪም የበጀት ምደባ ብቻ ሳይሆን አፈፃፀሙ በሥርዓተ-ጾታ መነፅር በትክክል መዳሰስ እና መገምገም ያስፈልጋል፡ ፡ እንዲሁም የፊስካል ፖሊሲ በተለይም ግብር፣ የመንግሥት እና የግል አጋርነት (PPP) በሥርአተ-ጾታ ላይ እስካሁን ድረስ ገለልተኛ (gender neutral ) ሆኖ ቆይቷል፡፡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ አብዛኛው ሠራተኞች የሥርዓተ-ጾታ ሥራን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለማቀናጀት አስፈላጊ የሆኑ የሥርዓተ-ጾታ ጥልቅ ዕውቀት፣ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት፣ የሥርዓተ-ጾታ ክስተት ትንተና ወይም ማንኛውንም የሥርዓተ-ጾታ ጥናት ክህሎቶች የላቸውም፡፡ በሥርአተ-ጾታ፣ በሥርአተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት እና ሥርዓተ-ጾታን ማካተት በፕሮፌሽናል ሰራተኞች፣ በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ ያሉ አመራር ላይ የሚገኙ ሴት ፕሮፌሽናል ሰራተኞችን በተመለከተ ያለው የተዛባ አመለካከት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያጋጠመው ሌላኛው በጎ ያልሆነ ሁኔታ ነው፡፡ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን እና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ቁርጠኝነትን በተገቢው ሁኔታ አለመመልከት ብሎም በትብብር አለመስራት ሌላው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ እየታየ ያለ ቁልፍ ክፍተት በመሆኑ ከፍተኛ ለውጥ የሚያስፈልገው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለው ተሳትፎና እገዛ የሚያረጋገጥ በየዘርፉ የትብብር መድረክን በተቋም፣ በማህበራት/በቡድኖች እንዲሁም በግለሰብ/በባለሙያ ደረጃ ለማቋቋም የገንዘብ ሚኒስቴር የመሪነቱን ሚና ይወስዳል፡፡

# 06.

## የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ- ዋና ምሰሶዎች፣ የሚጠበቁ ውጤቶች እና ቁልፍ ጣልቃ ገብነቶች/አቅጣጫዎች/ እርምጃዎች

ይህ ክፍል በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የቀረቡትን ስትራቴጂያዊ ጣልቃ ገብነቶች እንዲሁም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ተልእኮ ያካተተ ተቋማዊ አሠራሮችን ዝርዝር ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ስትራቴጂው በስድስት ዋና ዋና ምሰሶዎች ስር የተደራጁ ተቋማዊ ተልእኮዎችን እንዲሁም የሚኒስቴሩ የአሠራር መመሪያዎችን ተከትሏል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋና ዋና የፕሮግራም ተግባራት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ፅንሰ-ሀሳብን ለመቅረፅ ይረዳል፣ በመጨረሻም ከሌሎች የፕሮግራም ስራዎች ጋር በትይዩ ለውጡን ለመከታተል ይረዳል፡፡ የምሰሶቹ ገለፃ፣ የሚጠበቁ ውጤቶች እና የቁልፍ ጣልቃገብነቶች /አቅጣጫዎች/እርምጃዎች/ ከዚህ በታች በዝርዝር ተገልፀዋል፡፡

## 6.1 እስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች

የገንዘብ ሚኒስቴርን ከዚህ ቀደም ያለው ተሞክሮ የተሰጠውን ተልእኮ ከማሳካት አንጻር ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክርና ተሳትፎ እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶች ውስጣዊና ውጫዊ አካባቢን በመተንተን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን በጥብቅ በመፈተሽ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ ስትራቴጂያዊ ጎኖች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች እንዲካተቱ አስችሏል፡፡

- **የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን ማዕከል ያደረገ አገልግሎት አሰጣጥ (Gender sensitive service provision) በተቋሙ ውስጥ እና በተቋማዊ መዋቅሮች ውስጥ**

የገንዘብ ሚኒስቴር እንደ ዋና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የበጀት ፖሊሲን መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ፣ የኢኮኖሚ ትብብርን ማጠናከር፣ የመንግሥት በጀት መመደብ እና ማስተዳደር፣ የየመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር (PFM) ስርዓት መዘርጋት፣ የውጭ ሀብቶችን የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን ማሰባሰብ እና ማስተዳደር እንዲሁም ሥርዓተ-ጾታን ማዕከል ያደረገ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና እና የሚደረጉ ክንውኖች ውጤታማ እና ብቁ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ማስቻል ከተሰጠው ተልእኮ አንፃር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም በሁሉም ደረጃዎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት አጀንዳን በሀገር ደረጃ እውን ለማድረግ ይረዳል፡፡ ስለሆነም ገንዘብ ሚኒስቴር የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ በራሱ እና በሥሩ ባሉ ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ግንባር ቀደም መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡

- **ከሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር በማክሮ ኢኮኖሚ እና በፊስካል ጉዳዮች ልማት ላይ ያተኮረ የጋራ መድረክ**

የገንዘብ ሚኒስቴር ማዕከላዊ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እንደመሆኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን በማክሮ ኢኮኖሚ እና በፊስካል ዘርፍ ለማብቃት የሚያግዝ የተጠናከረ፣ የተቀናጀ፣ በህግ የተወሰነ እና በስምምነት የሚደረግ የጋራ መድረክ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግታት ጋር በሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ፖሊሲ ላይ የውይይት መድረክን በመደበኛነት ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ የመድረኩ መመስረትም የመረጃ እና የመረጃ ፍሰት በተቀላጠፈ መልኩ የሚከናወንበትን የክትትልና ግምገማ (M&E) ስርዓትን ለማጠናከር ይረዳል፡፡ የውይይት መድረኩ ከሥርዓተ-ፆታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት አፈፃፀም በተመለከተ የውስጥ እና በውስጥ ዲፓርትመንት/ተቋማዊ ግብረመልስ ዘዴን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ በዚህ ረገድ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በሊቀመንበርነት እና በጸሀፊነት ሆነው የሚያገለግሉበት የስትሪንግ እና የቴክኒክ ኮሚቴ መቋቋም ዘላቂ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት የተቋም መዋቅር መፍጠር ሂደቱን እና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በተከታታይ የሚወያዩበት መድረክ ለመፍጠር ያስችላቸዋል፡፡

- **የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የገንዘብ ፖሊሲ ቀረፃ እና አፈፃፀም**

የመንግስት በጀት እና የፊስካል በጀት እርምጃዎች የሴቶችን ልማት እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ የሥርዓተ-ጾታ በጀት ዝግጅት እንደ የገንዘብ ሚኒስቴር ያሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የግብር እና የወጪ ፖሊሲዎች እና/ወይም የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር መሳሪያዎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ላይ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሴቶች ልህቀትን በሁሉም ረገድ ለማረጋገጥ ያስችላቸዋል፡፡ ስለሆነም የፊስካል ፖሊሲ ዝግጅት እና አተገባበር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሥርዓተ-ጾታ አተገባበር እና አፈፃፀም በማረጋገጥ በመጨረሻም ፍትሃዊ ህብረተሰብን ለመፍጠር ያስችለዋል፡፡ በተመሳሳይ የትኛውም የፊስካል ፖሊሲ ትንተና እርምጃዎች ከመወሰዱ በፊት የፊስካል ፖሊሲ ዝግጅትና አፈጻጸም የሥርዓተ-ጾታ መነፅር ሊኖረው ይገባል፡፡

ሌላው ዋና ምሰሶ (sub-pillar) የሆነው የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ጥሪ ሰርኩላር ዝግጅት፣ የበጀት መግለጫ፣ ለሥርዓተ-ጾታ የተለየ በጀት (sub-program-target level) ነው፡፡ የተሻሻለውን እና አጠቃላይ የተተገበረውን የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ለማሳደግ፣ በጀት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ጉልህ እና ወሳኝ ሚና አለው፣ ለዚህም በምክንያትነት የሚወሰደው የሥርዓተ-

ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት (GRB) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ዝግጅት ላይ ልዩ ትኩረት ይፈልጋል ። የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ግቦች እንዲሁም ከሀገራዊው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት አቅጣጫ እና እንደ የዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) ካሉ ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር አብሮ መሄድ አለባቸው። በመሆኑም የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ እና ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ (GES) ጋር ያለው ትስስር የሚያሳይ ተጨማሪ ዝርዝር ዳሰሳ ማድረግ ያስፈልጋል።

- **የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ (Gender responsive) የመንግስት ፋይናንስ እና የወጪ ስርዓት ዝግጅትና አተገባበር**

ቀልጣፋ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በራሱ ግማሽ የሚሆኑ ሴቶች የሚገኙባቸውን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ይጠቅማል። ሆኖም የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ማስፈን በፍጥነት እንዲጓዝ የተዘጋጀው የሥርአተ-ጾታ ስትራቴጂ ጨምሮ እየተደረገ ያለው ከየመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ጋር የተያያዘ ማሻሻያ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ መሆን እንዳለበት መረጋገጥ አለበት። ስለሆነም የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ለGES ውጤታማ መሆን ቁልፍ ምሰሶ ነው።

- **የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የመንግሥትና የግል አጋርነት አሰራር**

የተለያዩ የመሠረተ ልማት አቅርቦቶች ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ ከባህላዊ ምንጭ ባሻገር አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ በተለይም የግሉን ዘርፍ በመንግስትና የግል አጋርነት (መግአ) ማዕቀፍ ተሳትፎ እንዲያደርግ መፈለግ ከምንጊዜውም በላይ አሁን ላይ ወሳኝ እየሆነ መጥቷል። እንዲህ ዓይነቱ የፖሊሲ አፈፃፀም ሴቶችን በተመጣጣኝነት ይጠቅማል። በዚህ መሰረት መንግስት ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በገንዘብ ሚኒስቴር መሪነት የመንግስትና የግል አጋርነት ፖሊሲ እና አዋጅ ተዘጋጀ። ሆኖም የመግአ ፖሊሲ እና በመግአ ለመተግበር የተለዩት ፕሮጀክቶች ስለ ሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ምንም የሚሉት ነገር ስለሌለ እንደዚህ ያሉ ፕሮጀክቶች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ሊከተሏቸው የሚገቡ እንደዚህ አይነት ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ። ስለሆነም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ሁሉም የመግአ ፕሮጀክቶች ከዲዛይን እስከ አተገባበር ድረስ ሥርዓተ-ጾታን ያማከሉ እና በተመሳሳይ ምላሽ የሚሰጡ መሆን አለባቸው።

- **የሥርዓተ-ጾታ አካታች የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች**

በኢኮኖሚ ትብብር እና ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ሀብት ድህነትን ለመቀነስና እና የሁሉንም ዜጎች በኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና ደህንነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ምንም እንኳን ከለኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት-ልማት እርዳታ ኮሚቴ (OECD-DAC) አባላት የሚሰጠው እርዳታ በአብዛኛው የሥርአተ ፆታ ዒላማዎች አካታች ቢሆንም (በአተገባበሩ ላይ አሁንም ትልቅ ክፍተት አለው) በተለይ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አባላት ካልሆኑ የልማት አጋሮች የሚገኙ ኮንሴሽናል ብድሮች እና ዕርዳታ ላይ ክፍተት ይታያል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጭ የእርዳታ ውጤታማነትን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ለማረጋገጥ ያለውን ጠቀሜታ በመለየት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሥርአተ ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በኩል የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የውጭ ሀብት ማሰባሰብ ውጤታማነት እና ተጓዳኝ አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ እና መሳሪያ አዘጋጅቷል። ስለሆነም በሚቀጥለው የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ ትግበራ ጊዜ ውስጥ የትኛውም የኢኮኖሚያዊ ትብብር የሥርዓተ-ጾታን ያካተተ መሆን አለበት።

- **የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እና የገንዘብ ሚኒስቴርን የተቋም እና የማስፈፀም አቅም ማሻሻል**

የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ንቅናቄ ዘመቻን የመምራት ሃላፊነት አለበት። የዳይሬክቶሬቱን የሰው ኃይልና የመፈጸም አቅም በማሳደግ ጠንካራ አፈፃፀም እና የአተገባበር አቅም መገንባት ሁሉን አካታች ልማት ለማጎልበት እጅግ አስፈላጊ ነው። መደበኛ የመማር እና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት ለሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ሰራተኞች እና ለሌሎች የገንዘብ ሚኒስቴር ሰራተኞች በመደበኛነት የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን በዕለት ተዕለት ሥራቸው ለማካተት የሚያግዝ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ዳይሬክቶሬቱን እና ሚኒስቴር መ/ቤቱን ለጠናከር የሥርዓተ-ጾታ ልዩ ባለሙያዎችን እና አማካሪዎችን ቅጥር ማከናወን ያስፈልጋል።

- **በሥርዓተ-ጾታ የተከፋፈለ የክትትልና ግምገማ (M&E) እና የመረጃ ስርዓት**

የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ውጤታማ አፈፃፀም እና በተወሰነ ማዕቀፍ ውስጥ መካተቱን ለመከታተል የሚያስችል እጅግ አስፈላጊ የመከታተያ ሥርዓት ነው። ውጤታማ የክትትልና

ግምገማ ሥርዓት በጾታ እና በሥርአተ-ጾታ በተከፋፈለ መረጃ እና በመረጃ ስርዓት ላይ የተገነባ መሆን አለበት። ስለሆነም የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት እና ገንዘብ ሚኒስቴር በሚኒስቴሩ ውስጥም ሆነ ውጫ ለሚከናወኑ ትግበራዎች ተገቢውን ክትትል እና የአተገባበር ግብረ-መልሶችን ለመመልከት የሚያስችል የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት (one-stop information system) ለመዘርጋት በጋራ መስራት አለባቸው።

**ዓላማ 1: - በተቋሙ ውስጥ እና በተቋማዊ መዋቅሮች ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ አገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ**

## 1.1. የተሻሻለ የሴቶች አቅም እና ብቃት በተቋሙ ውስጥ

- የሴቶች ሰራተኞችን የአቅም ክፍተት ዳሰሳ ማካሄድ እና ዋና የአቅም ክፍተቶችን መለየት፣
- በተለዩት ክፍተቶች ላይ በመመርኮዝ በተቋሙ ውስጥ ላሉ ሴት ሠራተኞች የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን እና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማመቻቸት፣
- በተቋሙ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ለሰራተኞች ማዘጋጀት፣
- በታቀዱ ተግባራት ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ዒላማዎችን ማካተት እና ሴት ሰራተኞችን በአመራር ቦታ ላይ ማብቃት።

## 1.2. በተቋሙ ውስጥ ላሉ ሴት ሠራተኞች የተፈጠረ ምቹ የሥራ ከባቢ

- የህጻናትን ማቆያዎችን አስፈላጊ በሆኑ መሳሪያዎችና የሰው ኃይል ማሟላት፣
- የህጻናትን ማቆያ ያለውን የአገልግሎት አቅርቦትና ጥራትን በየጊዜው መከታተል፣
- በተቀዋሙ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት አጀንዳ በተሻለ ሁኔታ ለማንፀባረቅ የመስሪያ ቤቱን የሰው ኃይል (HR) ስትራቴጂ መዳሰስ እና መከለስ፣
- በተቋሙ ውስጥ የሴቶችን አቅም እና ብቃት የሚያበረታቱ የተለያዩ ስታንዳርዶችን፣ መመሪያዎችን፣ እና ጋይድ ላይኖችን ማዘጋጀት እና ተግባራዊነታቸውን መከታተል።

**ዓላማ 2- ከሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር በማክሮ ኢኮኖሚ እና በፊስካል ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የጋራ መድረክ መፍጠር**

- ከባለበጀትና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነትና ሴቶችን በኢኮኖሚ ማብቃት፣ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት የሚሰጡ የፖሊሲ ውይይቶችን በመደበኛነት ለማካሄድ የውይይት መድረክ መፍጠር/ማጠናከር፣
- የባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና የክልል መንግስታት በመደበኛነት ለሥርአተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አተገባበርና አፈፃፀም ሪፖርቶችን የሚያቀርቡበት ስርዓትን ማጠናከር፣
- የሥርዓተ-ጾታ ሥራዎችን አፈፃፀም በተመለከተ የውስጥ ዲፓርትመንት/ ተቋማዊ ግብረመልስ ዘዴን መደገፍ።

ዓላማ 3- የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፊስካል ፖሊሲ ቀረፃን እና አተገባበሩን ማረጋገጥ

## 3.1 የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶችን እና ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን ለመፍታት የፋይናንስ ፖሊሲዎች፣ ማሻሻያዎች እና የሕግ ማዕቀፎች ተዳሰዋል፣ ተሻሽለዋል።

- በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ መሳተፍ እና የሴቶችን ፍላጎት በተሻለ የሚያንፀባርቁ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ግብዓቶችን ማቅረብ፣
- አሁን በተግባር ላይ ያለውን የፋይናንስ ፖሊሲዎችን እና የሕግ ማዕቀፎችን በመገምገም በውስጡ ያሉ ዋና ዋና ክፍተቶችን በመለየት በፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣
- የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፊስካል ፖሊሲዎችን ከተገበሩና ውጤታማ ከሆኑ ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይነት ካላቸው ሀገሮች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቅሰም ለወደፊት የፖሊሲ ዝግጅት ተሞክሮዎችን መውሰድ።

## 3.2. አሁን በሥራ ላይ ባሉት የተለያዩ የፋይናንስ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ከሥርአተ-ጾታ አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ የታዩ ክፍተቶችን ለመለየት መደበኛ ዳሰሳዎች ተደርገዋል

- ግብር በሴቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመዳሰስ የታክስ ሁነት ትንተና ማካሄድ እና መፍትሄውን መጠቀም፣
- አሁን ባለው የበጀት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት ከሚመለከታቸው የዘርፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር መደበኛ ውይይቶችን ማካሄድ፣
- በአገሪቱ ውስጥ ላሉት የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶች በተሻለ ምላሽ የሚሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎችን እና የፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብ፡ ፡

ዓላማ 4 የሥርዓተ-ጾታ ትክክለኛ ምላሽ ሰጭ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር እና የበጀት ወጪ ስርዓት

## 4.1 የተሻሻለ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት ዝግጅት፣

- የባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እና የክልል መንግስታት ዓመታዊ የበጀት ዝግጅት ማቅረቢያዎችን መከለስ፣
- ዓመታዊው የበጀት ዝግጅት ማቅረቢያ ከከሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ፣
- በአመታዊ በጀት መስሚያ ወቅት ሴቶችን ከማብቃት አንጻር የሚጠቅሙ ግልፅና ሊተገበሩ የሚችሉ አስተያየቶችን ወይም ግብረመልስ መስጠት፣
- የሥርዓተ-ጾታ ዒላማዎችን በዓመታዊ ዕቅዶች እና በፕሮግራም በጀቶች ውስጥ ማካተት፣
- ሴቶችን የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራት የበጀት ምደባ እንዲጨምር ግፊት ማድረግ፣
- የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት።

## 4.2 ውጤታማ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ምደባ እና አጠቃቀም ዘዴዎች መኖር

- በሥርዓተ-ጾታ የተከፋፈሉ የመንግሥት ወጪ ጠቀሜታ ትንተና ማካሄድ፣
- የፕሮጀክቶች ክትትልና ትግበራ አፈጻጸም ከሴቶች ተጠቃሚነት ጋር በተመለከተ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ
- የፕሮግራም በጀት አተገባበር እና አጠቃቀም ላይ መመሪያዎችን እና ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣
- ከሥርዓተ-ጾታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት እና የተመደቡ በጀቶች ውጤታማ አጠቃቀም ላይ መደበኛ ክትትል ማካሄድ፣
- በፕሮግራም በጀት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዋና አጀንዳ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

**ዓላማ 5 በመንግሥትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎን ማጠናከር**

## 5.1 በመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ውስጥ የተሻሻለ የሴት ሥራ ፈጠራ ባለቤቶች ተሳትፎ

- ሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP) ፕሮጄክቶች ውስጥ እንዲሳተፉ የግንዘቤ ፈጠራ መድረኮችን ማካሄድ፣
- ሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስት እና በግል አጋርነት ፕሮጄክቶች ላይ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለመደገፍ እንዲቻል ከዘርፍ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በትብብር መሥራት፣
- የሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጄክቶች ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ የአቅም ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣
- በተለዩት የአቅም ክፍተቶች መሰረት ለሴት ሥራ ፈጣሪዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን።

## 5.2 በመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴት ሥራ ፈጣሪዎች ውጤታማ ተሳትፎን በሚያመጡ የድጋፍ ማሻሻያዎች መኖር

- የሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ተሳትፎ እና ትግበራ ላይ የሚያጋጥሟቸውን ማነቆዎች መዳሰስ፣
- ከግል ዘርፍ ድርጅቶች ጋር በጥብቅ በመተባበር የመንግሥት እና የግል ዘርፍ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- በመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጄክቶች ውስጥ የሴት ሥራ ፈጣሪዎችን ውጤታማ ተሳትፎ የሚያሳድጉ የሪፎርም ሥራዎች እንዲሰሩ ግፊት ማድረግ፣
- የተለያዩ ማሻሻያዎችን አፈፃፀም መከታተል፡

**ዓላማ 6 የሥርዓተ-ጾታን ያካተተ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች፡**

## 6.1. ቁጥሩ የጨመረ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጭ የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች

- በኢኮኖሚ ትብብር ውይይቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ፣
- የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች ግምገማ ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ አመለካከቶችን ማንጸባረቅ፣
- የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የኢኮኖሚ ትብብሮች አስፈላጊነት ላይ ለመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት/ ፈራሚዎች የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የውጭ ሀብት ማሰባሰብ እና ድርድር ላይ፣ በፕሮግራም ዲዛይን፣ በፕሮጀክት ዝግጅት፣ በልማት አጋሮች ፋይናንስ በሚደረጉ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡፡

## 6.2. መጠኑ የጨመረ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጭ ተግባራት የተመደበ የODA የሀብት እቅድ

- የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች በODA የፍሰት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ ክትትል ማድረግ፣
- ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ተግባራት የሚመደበው ፋይናንስ እንዲጨምር በበጀት ፍሰት ላይ ግፊት ማድረግ፣
- የODA ዕቅድ አፈፃፀም እና የበጀት ወጪ አጠቃቀም ሪፖርቶች ከሥርዓተ-ጾታ አንጻር መተግበራቸቸውን መከታተል፡፡

**ዓላማ 7 የተዘረጋ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ እንዲሁም የሪፖርት ስርዓት**

## 7.1. በገንዘብ ሚኒስቴር እና በአጋር ተቋማት ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ተያያዥ ጉዳዮች አፈፃፀም ለመከታተል የተቋቋመ ውጤታማ የክትትልና ግምገማ (M&E) ስርዓት

- የሥርዓተ-ጾታን የተመለከቱ የእቅድ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመከታተል የሚያስችል የተለያዩ የM&E ማንዋሎችን እና መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣
- ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ ለመከታተል እንዲቻል የታቀዱት ተግባራት SMART መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- በተቋሙ ውስጥ እንዲሁም ከባለበጀት እና ከክልል አጋር ድርጅቶች ጋር በጥሩ ሁኔታ የተጣጣሙ፣ በመደበኛ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ፣ በጾታ የተከፋፈለ የሪፖርት እና ግብረመልስ ዘዴ ማቋቋም፣
- በተቋሙ ውስጥ እንዲሁም ከባለበጀት እና ከክልል አጋር ድርጅቶች ጋር የጋራ የግምገማ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- በሥርዓተ-ጾታ የተከፋፈሉ የመንግሥት ወጪዎችን መረጃ መከታተያ ሥርዓት መዘርጋት፡፡

## 7.2. የአፈፃፀም ሪፖርቶች በደንብ ተገምግመው የተዘረጋ የተጠያቂነት ስርዓት

- መደበኛ የሥርዓተ-ጾታ አፈፃፀም ኦዲት ማካሄድ፣
- በጥናት በተለዩ ዋና ዋና ክፍተቶች ላይ ከመምሪያዎች፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል ቢሮዎች ጋር መደበኛ ውይይት ማካሄድ እና የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማ የሆነ የM&E ሥርዓትን ለማጎልበት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

## RESULT FRAMEWORK

## ስትራቴጂክ ዓላማዎች፣ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና አመልካቾች

| ውጤት/ ስትራቴጂክ አላማዎች | የሚጠበቁ ውጤቶች | ዋና ዋና ተግባራት | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| Impact: ሴቶች በሀገሪቱ የፊስካል ፖሊሲዎች ትግበራ እንዲሁም የፐብሊክ ፋይናንስ ክፍፍል እና አጠቃቀም ላይ እኩል ተጠቃሚ ናቸው | | | |
| አላማ 1: በተቋሙ ውስጥ እና በተቋማዊ መዋቅሮች ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የአገልግሎት አቅርቦትን ማሻሻል | 1.1 የተገነባ የሴቶች አቅም እና ብቃት በተቋሙ ውስጥ | ■ የሴት ሰራተኞችን የአቅም ክፍተት ምዘና ማካሄድ እና ዋና የአቅም ክፍተቶችን መለየት<br>■ በተለዩት የአቅም ክፍተቶች ላይ በመመርኮዝ በተቋሙ ውስጥ ላሉ ሴት ሰራተኞች የተለያዩ ስልጠናዎችን እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማመቻቸት<br>■ ለተቋሙ ሰራተኞች የጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት<br>■ በታቀዱ ተግባራት ውስጥ የሥርዓተ-ጾታ ዒላማዎችን ማካተት እና ሴት ሰራተኞችን በአመራር ቦታ ላይ እንዲሰተፉ ማስቻል | ■ ለውስጥ ሰራተኞች የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት<br>■ የሰለጠኑ የሴት የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ ስራተኞች ድርሻ በመቶኛ<br>■ የተዘጋጁ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ብዛት<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ዒላማዎችን አፈፃፀም በፐርሰንት |
| | 1.2 በተቋሙ ውስጥ ላሉ ሴት ሠራተኞች የተፈጠረ ምቹ የሥራ ሁኔታ | ■ በተቋሙ የሚገኘውን የህጻናት መንከባከቢያ ማዕከልን አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶችና በሰው ኃይል ማደራጀት<br>■ የሕጻናት ማቆያ ያለውን የአገልግሎት አቅርቦትና ጥራትን፣ ውጤታማነት በየጊዜው መከታተል<br>■ በተቋሙ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና የሴቶች ብቃት በተሻለ ሁኔታ እንዲንጸባረቅ የመስሪያ ቤቱን የሰው ኃይል የማብቃት አጀንዳ በመገምገም መከለስ ፡፡<br>■ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሴቶችን አቅም እና ብቃትን የየሚያበረታቱ የተለያዩ ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎችን እና ጋይድላይኖችን ማዘጋጀት | ■ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት የሚሰጥ የህጻናት እንክብካቤ ማዕከል<br>■ ተዘጋጅተው በትግበራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች ፣ ስታንዳርዶች እና መመሪያዎች ብዛት |
| | 1.3 የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የአገልግሎት አቅርቦቶችን ለማሳደግ ጠንካራ የውስጥ እና በውስጥ የሥራ ክፍሎች የትብብር መድረክ ተመስርቷል | ■ የአገልግሎት አቅርቦቶችን ከሥርዓተ-ጾታ እኩልነት አንጻር ስለመተግበራቸው ለመገምገም የሚያስችል መደበኛ የውይይት መድረኮችን በእያንዳንዱ የሥራ ክፍል ውስጥ ማጠናከር<br>■ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በመደበኛነት ለሥርዓት ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚያቀርብበትን የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን ማጠናከር | ■ የተካሄዱ የውይይት መድረኮች ብዛት<br>■ ተዘጋጅተው የቀረቡ ሪፖርቶች ብዛት |
| | 1.4 ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር የሥርዓት-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፖሊሲ ውይይቶችን እና የፖሊሲ አፈፃፀም እንቅስቃሴዎችን ለማመቻቸት ያለመ የጋራ መድረክ ተቋቁሟል ፡፡ | ■ ባለበጀትና የፌዴራል መ/ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ጋር የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትና ሴቶችን በኢኮኖሚ ማብቃት፣ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት የሚሰጡ የፖሊሲ ውይይቶችን በመደበኛነት ለማካሄድ የውይይት መድረክ መፍጠር/ ማጠናከር<br>■ የባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና የክልል መንግስታትን ከሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አተገባበርና አፈጻጸምም አንጻር በመደበኛነት ከሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የሚያቀርቡበት ሥርዓትን ሥርዓትን ማጠናከር<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ሥራዎችን አፈፃፀም በተመለከተ በዲፓርትመንቶችና በተቋሙ ውስጥ ተቋማዊ ግብረመልስ ዘዴን ማዳበር<br>■ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከታተል የሚያስችል እና ስርጭቱን ለመቀነስ የሚያግዝ መመሪያ ማዘጋጀት<br>■ በየሁለት ዓመቱ የሥርዓተ-ጾታ ኦዲት ሪፖርት እና ወቅታዊ የማድረግ ሥራ<br>■ ለሥርዓተ-ጾታ ኦዲት እና ወቅታዊ የማድረጊያ ስርዓት መዘርጋት | ■ የተካሄዱ የውይይት መድረኮች ብዛት በቁጥር<br>■ ተዘጋጅተው የቀረቡ ሪፖርቶች ብዛት በቁጥር<br>■ የተዘጋጁ ጋይድላይኖች ብዛት በቁጥር<br>■ የተካሄዱ የውይይት መድረኮች ብዛት በቁጥር<br>■ የተዘጋጁ ሪፖርቶች ብዛት በቁጥር<br>■ ለውስጥና ለውጭ ባለድርሻ አካላት የተዘጋጁ የስልጠና አውደ ጥናቶች ብዛት<br>■ የተለያዩ ክፍተቶች እና የትኩረት መስኮች ብዛት በቁጥር<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ኦዲት ግኝትን ተከትሎ የተፈቱ ጉዳዮች ብዛት በቁጥር |

| ውጤት/ ስትራቴጂክ አላማዎች | የሚጠበቁ ውጤቶች | ዋና ዋና ተግባራት | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| አላማ 2: ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር በጋራ በመሆን የሴቶችን አቅም ለመጠቀም በተለይም በማክሮ ኢኮኖሚ እና በፊስካል ጉዳዮች ልማት ላይ ያሉ በጋራ መስራት | 2.1 በፊስካል እና በኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ በተቀናጀ መልኩ የተጠናከረ የፖሊሲ ውይይት | ■ ከከባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጡ የፖሊሲ ውይይቶችን በመደበኛነት ለማካሄድ የሚረዳ የውይይት መድረክ ማቋቋም / ማጠናከር | ■ የተቋቋመ የቴክኒክ እና የስትሪንግ ኮሚቴዎች ቁጥር<br>■ የተካሄዱ መድረኮች ብዛት በቁጥር |
| | 2.2 የተሻሻለ ሪፖርት እና የሥራ ፍሰት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፤ ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና ከክልል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር | ■ የባለበጀት ሚኒስትሮች እና የክልል መንግስታት አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ መረጃን ለመለዋወጥ የሚያስችል ዘዴን የሚያዳብሩበት የሪፖርት አሰራርን ማጠናከር ፤ ጠንካራ የሪፖርት አሰራርን ማጎልበት<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ሥራዎችን አፈፃፀም በተመለከተ ውስጣዊ እና የውስጥ የሥራ ክፍል / ተቋማዊ ግብረመልስ ዘዴን ማጎልበት | |
| ዓላማ 3-የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፊስካል ፖሊሲ ዝግጅት እና ትግበራን ማረጋገጥ | 3.1 የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶችን እና ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን ለመፍታት የፊሲካል ፖሊሲዎች፣ ማሻሻያዎች እና የሕግ ማዕቀፎች አካታች እንዲሆኑ ተገምግመው ተሻሽለዋል ፡፡ | ■ በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ በመሳተፍ እና የሴቶችን ፍላጎት በተሻለ የሚያንፀባርቁ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ጉዳዮችን መለየትና መስጠት፣<br>■ ዋና ዋና ክፍተቶችን ለመለየት እና አሁን በተግባር ላይ ያለውን የፊሲካል የፖሊሲዎችን እና የሕግ ማዕቀፎችን በመገምገም በውስጡ ያሉ ዋና ዋና ክፍተቶችን በመለየት በፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የማሻሻያዎችን ሀሳብ ማቅረብ<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጭ የገንዘብ ፖሊሲዎችን በተሻለ ከሚተገብሩ ከሀገራችን ጋር ተመሳሳይነት ካላቸው ሀገሮች ምርጥ ልምዶችን በመቀመር ለወደፊት የፖሊሲ ዝግጅቶች ትምህርት መቅሰም ፡፡ | ■ ተሳትፎ የተደረገባቸው ወርክሾፖች ቁጥር<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ፖሊሲዎች ፣ ማሻሻያዎች እና የሕግ ማዕቀፎች ቁጥር<br>■ የተጠናቀሩ ምርጥ ልምዶች እና ተሞክሮዎች ቁጥር |
| | 3.2 የተለያዩ የፋይናንስ ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን ከሥርዓተ-ጾታ እይታ አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ክፍተቶችን ለመለየት መደበኛ ዳሰሳዎች ተከናውነዋል | ■ ግብር በሴቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመገምገም የታክስ ሁኔት ትንተና ማካሄድ እና መፍትሄ መጠቆም<br>■ አሁን ባለው የፊስካል ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት ከሚመለከታቸው የባለበጀት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር መደበኛ ውይይቶችን ማካሄድ ፤<br>■ በአገሪቱ ውስጥ ላሉት የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶች በተሻለ ምላሽ የሚሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎችን እና የተሻሉ የፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብ | ■ የዳሰሳ (assessment) ሪፖርት<br>■ ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና ከክልል መንግስታት ጋር የተደረጉ ውይይቶች ቁጥር<br>■ የተለዩ የፖሊሲ ክፍተቶች እና የቀረቡ የፖሊሲ አማራጮች |

| ውጤት/ ስትራቴጂክ አላማዎች | የሚጠበቁ ውጤቶች | ዋና ዋና ተግባራት | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| ዓላማ 4-የሥርዓተ-ጾታ ትክክለኛ ምላሽ ሰጭ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር እና የበጀት ወጪ ስርዓት | 4.1 የተሻሻለ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት ዝግጅት፣ | ■ የባለበጀት ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና የክልል መንግስታት ዓመታዊ የበጀት ማቅረቢያዎችን መከለስ<br>■ ዓመታዊው የበጀት ጥያቄ ማቅረቢያ ከሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት መሳርያ (tool) ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ<br>■ በዓመታዊ የበጀት መስሚያ ወቅት ሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ግልፅ የሆኑ ግብረመልስ ማቅረብ<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ዒላማዎች በዓመታዊ ዕቅዶች እና በፕሮግራም በጀቶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ<br>■ ሴቶችን በበለጠ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራት የበጀት ምደባ እንዲጨምር ክትትል ማደረግ<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መርሃ ግብር ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት | ■ ዓመታዊ በጀታቸው ተዳስሶ ግብረመልስ የቀረበባቸው ተቋማት ቁጥር፣<br>■ ሴቶችን በበለጠ ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ተግባራት የሚመደበው የበጀት መጠን ፤<br>■ በፕሮገራም በጀት ዝግጅት ላይ የተዘጋጁ ስልጠናዎች ቁጥር ፤ |
| | 4.2 የተዘረጋ ውጤታማ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ምደባ እና የአጠቃቀም ዘዴዎች | ■ በሥርዓተ-ጾታ የተከፋፈሉ የመንግሥት ወጪዎች እና ጥቅማጥቅሞች ሁነታዊ ትንተና ማካሄድ<br>■ የፕሮጀክቶች ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘትን ለሴቶች ከሚሰጡት ጥቅም ጋር በተመለከተ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>■ በሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የፕሮግራም በጀት አተገባበር እና አጠቃቀም ላይ መመሪያዎችን እና ጋይድ ላይኖችን ማዘጋጀት<br>■ ከሥርዓተ-ጾታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች አተገባበር እና የተመደቡ በጀቶችን ውጤታማ አጠቃቀም ላይ መደበኛ ክትትል ማካሄድ ፤<br>■ በፕሮግራም በጀት ፍኖተ-ካርታ (Road Map) ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዋና አጀንዳ መሆናቸውን ማረጋገጥ | ■ የተደረጉ ግምገማዎች ቁጥር<br>■ የተዘጋጁ ሪፖርቶች፣ መመሪያዎች እና ጋይድ ላይኖች ቁጥር<br>■ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ተግባራት የተመደበው የበጀት መጠን<br>■ PM&E ሪፖርቶች<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ አተገባበር roadmap |
| | 4.3 የተሻሻለ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጭ ፕሮግራም በጀት ዝግጅት | ■ ስለ ሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ቀጣይነት ያለው ስልጠና ማዘጋጀት<br>■ ተጠያቂነትን ለማሻሻልና ለማጎልበት እንዲሁም ኃላፊነትን የሚያጎለበት ስርዓት መዘርጋት<br>■ አሁን ያለውን የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ማንዋሎችን ፤ መመሪያዎችን እና ጋይድ ላይኖችን መከለስ<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ውጤታማነት እና ውጤታማ የመግቢያ ነጥብን (entry point) ለመከለስ የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ | ■ ለባበጀት ቢሮዎች የተሰጡ የ ሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ሥልጠናዎች ብዛት<br>■ የስልጠናዎች ውጤታማነት<br>■ ሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን በተመለከተ ተጠያቂነትን ለመፍጠር የተቋቋመ ስርዓት<br>■ በሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት እና በተዛማጅ ማሻሻያዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ብዛት |

| ውጤት/ ስትራቴጂክ አላማዎች | የሚጠበቁ ውጤቶች | ዋና ዋና ተግባራት | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| ዓላማ 5-በመንግሥትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎን ማጠናከር | 5.1 በ.PPP ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴት ሥራ ፈጣሪዎች ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል የተሻሻለ ምቹ የፖሊሲ አካባቢ መፍጠር | ■ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች በ PPP ፕሮጀክቶች ውስጥ እንዲሳተፉ የግንዘቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማካሄድ<br>■ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስትና በግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለመደገፍ እንዲቻል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ጋር በትብብር መስራት<br>■ የሴት ሥራ ፈጣሪዎች በመንግስት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች እንዲተገበሩ ግፊት ማድረግ<br>■ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን መከታተል<br>■ ከመንግስትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ጋር በመተባበር በመንግስት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ተሳትፎ ለሚያደርጉ የተለያዩ መ/ቤት ባለሙያዎች የሥርዓተ ጾታ ለውጥ አምጪ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት | ■ የተከናወኑ የግንዘቤ መፍጠሪያ ዝግጅቶች በቁጥር<br>■ የተዘረጋ የትብብር ግንኙነት እና የሪፖርት ስርዓት በቁጥር<br>■ የሴቶች ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የተዘረጋና የተዘጋጁ መድረኮች<br>■ የተዘረጋ የትብብር ግንኙነት እና የሪፖርት ዘዴ በቁጥር<br>■ የሴቶችን አቅም ለማጎልበት የተቋቋሙና የተካሄዱ መድረኮች ቁጥር<br>■ የተከናወኑ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ብዛት<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና መመሪያዎች ብዛት<br>■ የተዘጋጁ ሪፖርቶች ቁጥር |
| | 5.2 በ PPP ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴት ሥራ ፈጣሪዎች ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጡ የድጋፍ ማሻሻያዎች መተግበር | ■ የሴት ሥራ ፈጣሪዎች በPPP ፕሮጀክቶች ውስጥ ለመሳተፍ እና በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ማነቆዎች ለመፍታት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>■ የሴቶች ሥራ ፈጣሪዎች በPPP ፕሮጀክቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲሳተፉ ያሉባቸውን የአቅም ክፍተት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>■ በተለያዩ የአቅም ክፍተቶች ላይ በመመርኮዝ ለሴት ሥራ ፈጣሪዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማዘጋጀት<br>■ ከግል ዘርፍ አጋር ድርጅቶች ጋር በቅርብ በመተባበር የመንግሥትና የግል ዘርፍ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት | ■ የተዘጋጁ የግንዘቤ መፍጠሪያ መድረኮች<br>■ በሴቶች ሥራ ፈጣሪዎች ከሚተዳደሩ የመንግስት የግል አጋርነት |
| ዓላማ 6-የሥርዓተ-ጾታ አካታች የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች | 6.1 ቁጥሩ የጨመረ የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች የተነሱ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች | ■ በኢኮኖሚ ትብብር ውይይቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ<br>■ የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶችን በመገምገም የሥርዓተ-ጾታ አመላካከቶችን ማንጸባረቅ<br>■ የሥርዓተ-ጾታ ተኮር የኢኮኖሚያዊ ትብብር ስምምነቶች አስፈላጊነት በተመለከተ ለመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት / ፈራሚዎች የግንዘቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት | ■ ተሳትፎ የተደረገባቸው የውይይት መድረኮች ቁጥር<br>■ የተፈረሙ የሥርዓት ጾታ ተኮር የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነቶች ቁጥር<br>■ ስልጠና የወሰዱ የከፍተኛ ባለሥልጣናት ቁጥር |
| | 6..2 መጠኑ የጨመረ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ተግባራት የተመደበ የODA ዕቅድ | ■ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ኦፊሴላዊ የልማት እርዳታ (ODA) የፍሰት ዕቅዶች ውስጥ መካተታቸውን ክትትል ማድረግ<br>■ በበጀት አመዳደብ ሥርዓተ-ፆታ ተኮር ለሆኑ ተግባራት የፋይናንስ ምደባ እንዲጨምር ግፊት ማድረግ<br>■ የODA ዕቅዶች እና የበጀት ወጪ አጠቃቀም ሪፖርቶች ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር መተግበራቸውን መከታተል | ■ የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች ቁጥር<br>■ ለሥርዓተ-ጾታ ተኮር ተግባራት የተመደበው የODA መጠን |

| ውጤት/ ስትራቴጂክ አላማዎች | የሚጠበቁ ውጤቶች | ዋና ዋና ተግባራት | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| ዓላማ 7 ጠንካራ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 7.1 የሥርዓተ-ጾታ ነክ ዒላማዎችን አፈፃፀም ለመከታተል ውጤታማ የሆነ የ M&E ስርዓት በገንዘብ ሚኒስቴር እና በአጋር ድርጅቶች ውስጥ ተዘርግቷል | ■ የሥርዓተ-ጾታን የተመለከቱ የዕቅድ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመከታተል የሚያስችል የተለያዩ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶችን መዘረጋት<br>■ ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ ለመከታተል እንዲቻል የታቀዱት ተግባራት SMART መሆናቸውን ማረጋገጥ<br>■ በተቋሙ ውስጥ እንዲሁም ከባለበጀት እና ከክልል አጋር ድርጅቶች ጋር ጥሩ ሁኔታ የተጣጣሙ፣ በመደበኛ የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት፣ በጾታ የተከፋፈለ የሪፖርት እና ግብረ-መልስ ዘዴ ማቋቋም<br>■ በተቋሙ ውስጥ እንዲሁም ከባለበጀት እና በክልል አጋር ድርጅቶች ውስጥ የግምገማ መድረኮችን ማዘጋጀት<br>■ በስርዓተ-ፆታ የተከፋፈለ የመንግሥት ወጪ መረጃ መከታተያ ሥርዓት መዘርጋት | ■ የተዘጋጁ መመሪያዎች እና ጋይድላይኖች ቁጥር<br>■ የቀረቡ የM&E ሪፖርቶች ቁጥር<br>■ የተካሄዱ መደበኛ ውይይቶች ቁጥር<br>■ የተቋቋመ እና በተግባር ላይ የዋለ መረጃ መከታተያ ስርዓት |
| | 7.2 የአፈፃፀም ሪፖርቶች በጥልቀት ተገምግመው የተጠያቂነት ስርዓት ተዘርግቷል<br><br>7.3 የተጠናከረ ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢ | ■ መደበኛ የሥርዓተ-ጾታ አፈፃፀም ኦዲት ማድረግ<br>■ ከሥራ ክፍሎች፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል ቢሮዎች ጋር በዋና ዋና የተለዩ ክፍተቶች ላይ መደበኛ ውይይት ማካሄድ እና የማስተካከያ እርምጃዎችን መጠቆም፣<br>■ ተጠያቂነት እና ውጤታማ የሆነ የM&E ሥርዓት ለመፍጠር የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን<br>■ ሥርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት እና አተገባበሩን መከታተል<br>■ በሥርዓተ-ጾታ ኦዲት አማካኝነት ክፍተቶችን መለየት | ■ የሥርዓተ-ጾታ ኦዲት ሪፖርቶች እና የተለያዩ ክፍተቶች በቁጥር<br>■ የተካሄዱ ውይይቶች ቁጥር<br>■ የቀረቡ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ቁጥር |

# 07.

# ክትትል እና ግምገማ

የሥርዓተ-ጾታ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሁሉንም የመስሪያ ቤቱን ተግባራት በጥንቃቄ መስራት እንዲሁም በሁሉም ደረጃ በስራ ክፍሎች ውስጥ እና በስራ ክፍሎች መካከል የሥርዓተ-ጾታ ውጤቶችን መሰብሰብ አለባቸው፡ ፡ ይህ አካሄድ ዝርዝር በሁሉም ደረጃ የተካተቱ (ሜንስትሪምድ የሆኑ) የሥርዓተ-ጾታ ተግባራትን እና ውጤቶችን ለመለካት ያስችላል። የዕቅድ ትግበራ ላይ በጾታ በተከፋፈሉ መለኪያዎች ክትትል ይደረጋል። በመሆኑም የመነሻ፣ የአጋማሽ እና የመዝጊያ የግምገማ ጥናቶች እና በማንኛውም ተግባር ውጤትን በተገቢው መልኩ ለመከታተል የሚያገለግል በጾታ የተከፋፈለ መረጃ መዘጋጀት ይኖርበታል።

# 08.

# ግንኙነት

መረጃ ለሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ ወሳኝ መሳርያ ነው፡፡ በቀጣይ ትግበራ ወቅት ጠቃሚ ተሞክሮዎችን ለማጋራት የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሞ መደበኛ የመገናኛ መድረኮችን መፍጠር ወሳኝ ይሆናል፡፡ በስራ ክፍሉ የሚከናወኑ ሁነቶችን በዌብሳይት እና በማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት የተለያዩ ግብአቶችን በድጋሚ ለማግኘት ይረዳል በተጨማሪም ግንኙነትን ያዳብራል፡፡ ይህም በተለያዩ ክፍሎች መካከል የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በሚመለከት ግንኙነትን ያሰልጣል፣ ከበላይ ኃላፊዎች ጋር ለመመካከር እና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ከዚህም በላይ ሥርዓተ-ጾታን የሚያሻግር አሰራር ለመፍጠር ያግዛል፡፡

# በስትራቴጂው የባለድርሻ አካላት ዝርዝር

| | የባለድርሻ አካል | አስተያየት |
|---|---|---|
| የውስጥ | የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት | |
| | የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር | |
| | የፊስካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት | |
| | የታክስ ፖሊሲ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | |
| | የግል እና የመንግስት ሽርክና | |
| | የስትራቴጂ ዕቅድ እና ማኔጅመንት | |
| | ለውጥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | |
| | የቻናል አንድ ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት | |
| | የመንግስት አካውንት ዳይሬክቶሬት | |
| | IFMIS ፕሮጀክት አስተዳደር | |
| | የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት | |
| | የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት | |
| | የመንግስት ወጪ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | |
| | ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ትብብር ዳይሬክቶሬት | |
| | መንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት | |
| | የብድር አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | |
| | የአውሮፓ ህብረት ትብብር ዳይሬክቶሬት | |
| | የተባበሩት መንግስታት፣ የአየር ለውጥ ፋሲሊቲ እና አህጉራዊ ትብብር ዳይሬክቶሬት | |
| | የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | |

| | |
|---|---|
| የውጭ | የፕላን እና ልማት ኮሚሽን |
| | የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ |
| | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን |
| | የትራንስፖርት ሚኒስቴር |
| | የሳይንስ እና የኢኖቬሽን ሚኒስቴር |
| | የከተማ ልማት እና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር |
| | የፌደራል የከተማ ስራ ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ |
| | የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር |
| | የኢንቨስትመንት ኮሚሽን |
| | የግብርና ሚኒስቴር |
| | የገቢዎች ሚኒስቴር |
| | የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር |
| | የትምህርት ሚኒስቴር |
| | የሴቶች፣ ወጣቶች እና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | የጤና ሚኒስቴር |
| | የፌደራል አቃቤ ህግ |
| | የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ |
| | የፖሊሲ ጥናት ተቋም |
| | የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር |
| | የክልል መንግስታት |
| ቁልፍ የባለድርሻ አካላት | የፌደራል መንግስት |
| | ሴቶች፣ ወንዶች፣ ወንድ ልጆች እና ሴት ልጆች |
| | በሴቶች በባለቤትነት የተያዙ የንግድ ድርጅቶች |
| | ሴት የስራ ፈጣሪዎች |
| | UN Women |
| | የዓለም ባንክ |
| | ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት |
| | እንደ DFID እና USAID ያሉ የመንግስታት የትብብር ተቋማት |
| | UWCA |
| | CCRDA |

## ትርጉሞች

ሥርዓተ-ጾታ፡ ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ለሴቶች እና ወንዶች የሚሰጧቸው ሚናን የሚያመለክት ነው።

የሥርዓተ-ጾታ ፍትሃዊነት፡ በሴቶች እና በወንዶች መካከል በሀብት አመዳደብ እንዲሁም በዕድሎች መድሎ አለማድረግን ያመለክታል።

የሥርዓተ-ጾታ ዕኩልነት፡ ሴቶች እና ወንዶች ሙሉ የሰብዓዊ መብቶቻቸው እንዲከበር እኩል የሆነ ሁኔታዎች እንዲኖራቸው እና ከኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ልማዶች እኩል ድርሻ ማበርከትን እንዲሁም ተጠቃሚ መሆንን ያመለክታል።

ሥርዓተ-ጾታን ማካተት፡ በየደረጃው ግልፅ በሆነ መልኩ የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች በሁሉም የልማት ፖሊሲዎች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማካተትን ያመለክታል።

የሥርዓተ-ጾታ ግንኙነቶች፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች እና ወንዶችን የሚያገናኙ ንዑስ የማህበራዊ ግንኙነቶች ክፍል ሲሆን ይህም በፆታዎች መካከል አቅም እና የሀብት ክፍፍል ስርጭትን ይመለከታል።

ፆታዊ ሚና፡ በተወሰነ ባህል ውስጥ ለአንድ ጾታ ተገቢ ነው ተብሎ የታመነበት የማህበራዊ እና የባህሪ ልማድ ነው።

ሥርዓተ-ጾታን ያላማከለ (Gender-Blind)፡ በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ ሥርዓተ-ጾታ ያለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያለማስገባት።

ሥርዓተ-ጾታምላሽ፡ በሴቶች እና በወንዶች መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት።

ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ (Gender Sensitive)፡ የሥርዓተ-ጾታ ግንኙነት ውጤቶችን መረዳት፣ ማንጸባረቅ እና ውሳኔ መስጠት።

የሥርዓተ-ጾታ ኦዲት፡ ከሚና እና ከፖሊሲ አንፃር የሥርዓተ-ጾታ እና ሴቶችን ማብቃትን በሚመለከት ተጠያቂነትን የመመርመር ተግባር ነው።

የሥርዓተ-ጾታ ትንተና፡ የሴቶች ተጠቃሚነት ላይ እክል የሚፈጥሩ ችግሮችን ለመፍታት በሴቶች ፍላጎቶች እና ችግሮቻቸው ላይ መረጃዎችን ማሰባሰብ እና መተንተን።

በፆታ የተከፋፈለ መረጃ፡ በሴቶች እና በወንዶች፣ በወንድ ልጆች እና በልጃገረዶች መካከል በተወሰነ ጉዳይ ያሉ ልዩነቶችን በሚመለከት የተቀመጠ ቁጥራዊ መረጃ ነው።

በሥርዓተ-ጾታ የተከፋፈለ መረጃ፡ በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም በልጃገረዶችና በወንድ ልጆች መካከል ያለውን አንፃራዊ ሁኔታ በሚያሳይ እና በሚያነፃፅር መልኩ የተቀመጠ ቁጥራዊ ያልሆነ መረጃ ነው።

የሥርዓተ-ጾታ ልዩነት/ክፍተት፡ በሴቶች እና ወንዶች እንዲሁም በልጃገረዶች እና ወንድ ልጆች መካከል የሚገኙበትን ሁኔታ ወይም ሀብት አጠቃቀምን በሚመለከት የተወሰነ ልዩነትን ወይም አለመመጣጠንን ያመለክታል።

ስትራቴጂያዊ የሥርዓተ-ጾታ ፍላጎቶች፡ ለጨታ እኩልነት መሰረታዊ መነሻዎች የሆኑ በግልፅ የማይታዩ እና የረዥም ጊዜ ጉዳዮች ናቸው።

ሴቶችን ማብቃት፡ ከማህበራዊ እና ሥርዓተ-ጾታ ጋር በተገናኙ ችግሮች ዙሪያ የሴቶችን የኃላ ተሳትፎ ማሳደግ እንዲሁም የሴቶችን ብቁነት የማረጋገጥ ሂደት ነው።

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስትራቴጂ
ገንዘብ ሚኒስቴር (ገሚ)
2014-2018